# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 168 የካቲት 18 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## የኢትዮ-ሶማሊላንድ ስምምነት ስለምን ስጋት ሆኖ ታየ?

ገጽ 6









## ኢትዮጵያ ለአህጉሩና ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሰላምና መረጋጋት ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክታለች

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለአህጉሩና ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሰላምና መረጋጋት ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክታለች፤ እያበረከተችም ትገኛለች ሲሉ አምባሳደር ቆንጂት ስነጊዮርጊስ ተናገሩ።

አምባሳደር ቆንጂት ስነጊዮርጊስ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ አህጉራዊ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር ከምታደርገው ጥረት በተጨማሪ በአፍሪካ ኅብረትና በኢጋድ አማካኝነት ለአህጉሩና ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሰላምና መረጋጋት ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክታለች፤ እያበረከተችም ትገኛለች፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በተባበሩት

« ኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አምባሳደር ቆንጂት ስነጊዮርጊስ

## ኢትዮጵያውያን ህብረ ብሔራዊነታቸውን በዓድዋ ድል አስመስክረዋል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን ህብረ ብሔራዊነታቸውን ጠላትን በአንድነት ቆመው ተዋግተው ባሸነፉበት የዓድዋ ድል ማስመስከራቸውን ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በከሪ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል ሕዝቦች ሀገራቸውን ለማዳን በመዘጋጀታቸው፣ በአንድነት በተከፈለ መስዋዕትነት የተመዘገበ የሚያስደንቅና በአርአያነትም የሚጠቀስ ህብረ ብሔራዊ ድል ነው፡፡

በአራቱም አቅጣጫ ተዋጊዎች አንድም ሳይቀሩ ዓድዋ ላይ ተዋግተው ሲያሸንፉ ያስመሰከሩት ህብረ ብሔራዊነታቸውን ነው ያሉት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ፤ ዓድዋ ህብረ ብሔራዊነት የኢትዮጵያ የወደፊት አቅጣጫ መሆን እንዳለበት ትምህርት የተሰጠበት ነው ብለዋል፡፡

"አጥንታቸው አንድ ላይ ነው የተቀበረው፡፡ ኢትዮጵያውያን ዛሬም ሆነ ነገ ከህብረ ብሔራዊነት ውጪ ሌላ ምርጫ የለንም" ብለዋል፡፡

የዓድዋ ጦርነት የተካሄደው በ1888 ዓ.ም. በወቅቱ መሪ በነበሩት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመን መሆኑን ያወሱት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ፤ ከጦርነቱ በፊት አጼ ምኒልክ



ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)

« ኢትዮጵያውያን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## በመዲናዋ የተለያዩ ሕዝባዊ ውይይቶች ተካሄዱ

ገጽ 6






አቶ ፍቃዱ ደፈረስ

# ለ100 ሺህ የቡና አልሚ አርሶ አደሮች የመስክ ትምህርት እየተሰጠ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ለ100 ሺህ የቡና አልሚ አርሶ አደሮች የመስክ ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ደፈረስ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በቡና ምርትና ምርታማነት ላይ የአርሶ አደሮች ግንዛቤ እጥረት፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የተባዮች መስፋፋት፣ የአፈርና የደን ጥበቃ ሥራዎች በተገቢው መልኩ አለመሠራታቸው ተግዳሮት ሆነዋል።

የቡና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የአርሶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻልና ዘርፉን ለማጠናከር ለ100 ሺህ የቡና አልሚ አርሶ አደሮች የመስክ ትምህርት እየተሰጠ ነው ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ ይህም በሲዳማ ክልል፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ በደቡብ ምዕራብ ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአማራ ክልል ተግባራዊ እየተደረገ ነው ብለዋል።

የመስክ ትምህርቱን የሚሰጡ 864 ሠራተኞችና ባለሙያዎች ለቡና አልሚ አርሶአደሮቹ የሚሰጡትን ትምህርት በሚመለከት ስልጠና ተሰጥቷቸው ወደተግባር ገብተዋል ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ የቡና አርሶ አደሮቹ በመስክ ትምህርቱ ከቡና አተካከል እስከ ምርት መሰብሰብ ያለውን ሂደትና ሳይንሳዊ ዘዴዎችን እንዲማሩ ይደረጋል ብለዋል።

የመስክ ትምህርቱ ለአንድ ዓመት የሚሰጥ ሲሆን፤ በዚህም ተግባራዊ ልምምድ እና ከሌሎች የቡና አልሚ አርሶ አደሮች ጋር የልምድ ልውውጥ እንደሚያደርጉ የገለጹት አቶ ፍቃዱ፤ ከመስክ ትምህርቱ ያገኙትን ግንዛቤ ለማወቅና ለመለካት የመውጫ ፈተና እንዲፈተኑ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ፍቃዱ ገለፃ፤ ፈተናውን ያለፉት የመስክ ትምህርቱን ማጠናቀቃቸውን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ሲሆን፤ ያላለፉት አርሶ አደሮች ደግሞ ትምህርቱን በድጋሚ እንዲከታተሉ ይደረጋል።

አቶ ፍቃዱ እንዳሉት፤ በ2014 ዓመተ ምህረት 100 ሺህ የቡና አልሚ አርሶ አደሮች የመስክ ትምህርቱን አጠናቀዋል። በዘንድሮ ዓመት ደግሞ ቁጥሩን 200 ሺህ እንዲደርስ ይደረጋል። ይህንን በማጠናከር ሁሉም የቡና አልሚ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሠራል።

አሁን ላይ በሀገሪቱ ከአንድ ሄክታር ከ6 እስከ 7 ኩንታል ቡና እየተመረ ይገኛል። ይህንን እስከ 2022 ዓመተ ምህረት ድረስ 12 ኩንታል ለማድረስ እየተሠራ እንደሆነም ገልጸዋል።

# በክልሉ በትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ከ432 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል

## - 49 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ተሠርተዋል
## - 39 አዳዲስ ቤተ መጻሕፍት ተገንብተዋል

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

ሀዋሳ፡- በሲዳማ ክልል ባለፉት ስድስት ወራት በተካሄደው የትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ከተለያዩ አካላት ከ432 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ማሰባሰብ መቻሉ ተገለጸ፡፡

የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድርና የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በየነ በራሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የገንዘብ መጠኑ ንቅናቄው ከተጀመረ አንስቶ በዓይነትና በጉልበት የተደረገውን ድጋፍ ጭምር የሚያካትት ነው፡፡

በክልሉ ቀደም ብሎ የትምህርት ተሐድሶ ፕሮግራም ተዘርግቶ ቋሚ የገቢ ምንጭ እንዲኖርና የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅ የሚያስችሉ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውን ኃላፊው አስታውሰዋል፡፡

የትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተጀመረ በኋላም የንቅናቄ ሥራው ከክልላዊ ፕሮግራሙ ጋር ተቀናጅቶ መቀጠሉን የተናገሩት ኃላፊው፤ በ2015 ዓ.ም ሐምሌ ወር በተጀመረው ንቅናቄ በክልሉ የተለያዩ ባለሀብቶች ራሳቸውን ችለው አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን መገንባት መቻላቸውንም አስታውቀዋል፡፡

ኃላፊው እንደገለጹት፤ በንቅናቄው 49 የሚሆኑ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በገጠራማ አካባቢዎች መገንባት የተቻለ ሲሆን፤ አንድ ባለሀብት ብቻውን በመሆን አዲስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መገንባት ችሏል፡፡

በግንባታ ሂደቱ 273 አዳዲስ የመማሪያ ክፍሎች ሲሠሩ፣ 3ሺ 770 የሚሆኑ ክፍሎች ደግሞ እድሳት ተደርጎላቸዋል፡፡ በተጨማሪም 39 አዲስ ቤተ መጻሕፍት የተገነቡ ሲሆን፤ 248 ነባር ቤተመጻሕፍቶች እድሳት ተደርጎላቸዋል፤ 34 አዳዲስ የውሃ መስመሮችንም መዘርጋት ተችሏል፡፡



አቶ በየነ በራሳ

አዳዲስ የተሠሩትና ነባር ትምህርት ቤቶች ላይ የተገነቡትን ጨምሮ 297 አዲስ የተማሪዎች መጸዳጃ ቤቶች ሲሠሩ፣ 240 ያህሉ እድሳት ተደርጎላቸዋል፡፡

ከግንባታ ሥራው በተጨማሪ የትምህርት ግብዓቶችንም የማሟላት ሥራ መሠራቱን ያመላከቱት የቢሮ ኃላፊው፤ ክልሉ ገዝቶ ያቀረበውን ሳይጨምር በንቅናቄው 13ሺ 619 የተማሪ መቀመጫዎች በሕዝብ ተሳትፎ ለተማሪዎች እንዲደርሱ መደረጉንም ገልጸዋል፡፡

36ሺ መቀመጫዎች እድሳት ተደርጎላቸው ተማሪዎች እየተገለገሉባቸው የሚገኝ ሲሆን፤ አዳዲስ የጥቁር ሰሌዳ ግዢና ነባሮቹን የማደስ እንዲሁም ሌሎች በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

በንቅናቄው ባለፉት ስድስት ወራት የትምህርት ቤቶችን የቅደመ ሁኔታ መቀየር መቻሉን ያመላከቱት ኃላፊው፣ ባለፉት ስድስት ወራት የተሠራና የተገኘውን በመገምገም እስከያዝነው ዓመት መጨረሻ ድረስ በንቅናቄው ለመዝለቅ አቅጣጫዎች ተቀምጠው ሥራው መቀጠሉን አስታውቀዋል፡፡

በቀጣይም በንቅናቄው የትምህርት ቤቶችን ገጽታ መቀየርና የተማሪ ውጤት ላይ ለውጥ ማምጣት እንደ አቅጣጫ ተቀምጠው ኅብረተሰቡን የማስተባበር ሥራው እንደሚቀጥል ጠቁመዋል፡፡

የትምህርት ስኬታማነት የሚለካው በተማሪው ውጤታማነት ነው ያሉት ኃላፊው፤ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ የሚሆኑት ትምህርት ቤቶቻቸው ውብና ሳቢ ሲሆኑ ነው ብለዋል፡፡

የተጀመረው ንቅናቄ ለተማሪዎች ውጤታማነትና የትምህርት ዘርፉን ለማሻሻል ለተያዘው እቅድ ወሳኝ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

ንቅናቄው አንዴ ተጀምሮ የሚያበቃ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው ነው በማለት ኅብረተሰቡ ለትምህርቱ ዘርፍ እያደረገ ላለው ድጋፍና ተሳትፎ አመስግነው ለዘርፉ ተሐድሶ ኅብረተሰቡ ተሳትፎውን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል፡፡

# በክልሉ በስድስት ወራት ውስጥ ከ5 ሺህ በላይ ሰዎች በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ተይዘዋል

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ ከ5 ሺህ በላይ ሰዎች በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ መያዛቸውን የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ አስታወቀ። 158 ሺህ ሰዎች ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ይገኛል ተብሎ እንደሚታሰብም ተጠቁሟል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ እና የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ኃላፊ ጉሻ በለኮ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በስድስት ወራት ውስጥ 1 ነጥብ 9 ሚሊዮን የማህበረሰብ ክፍሎች የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ምርመራ ተደርጓል።

በግማሽ ዓመት ውስጥ ከተመረመሩት ውስጥ 5 ሺህ 500 ያህል ሰዎች የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ተገኝቷል።

ይህ ቁጥር ዜሮ ነጥብ 34 በመቶ ስርጭት መጠን የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሰው፤ 5 ሺህ 200 የሚሆኑት መድኃኒት የጀመሩ መሆኑን አስታውቀዋል።

ዶክተር ጉሻ እንደገለጹት፤ እንደ ክልል በአጠቃላይ 158 ሺህ የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ይገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በክልሉ ከሚገኙ አጠቃላይ በቫይረሱ ከተያዙት ሰዎች ውስጥ 127 ሺህ የሚሆኑት መድኃኒት ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፤ ከነዚህ መድኃኒት ተጠቃሚዎች 97 በመቶ የሚሆኑት በደማቸው ያለው የቫይረስ መጠን በሚፈለገው ልክ ዝቅ ብሎላቸዋል ብለዋል፡፡

ይህ ማለት ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ቢኖርም እንደማንኛውም ሰው የራሳቸውን ኑሮ ማካሄድና ልማት ውስጥ መሳተፍ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ ተጋላጭነት ቢኖርም የበሽታው የመተላለፍ ዕድልን የሚቀንስ መሆኑን አስታውቀዋል።

ኃላፊው በኦሮሚያ ክልል ያለው የስርጭት ምጣኔ ወደ 0ነጥብ 6 በመቶ ሲሆን፤ እንደ አዳማ፣ ሻሸመኔ፣ ጅማ እና ቢሾፍቱ ያሉ ከተማዎች ላይ የስርጭት ምጣኔው እስከ 3 በመቶ ከፍ ያለ ይሆናል ብለዋል፡፡

ለበሽታው ከ18 እስከ 28 ዓመት በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች፣ ሆቴል አካባቢ የሚሠሩ ሠራተኞች እና ሹፌሮች ይበልጥ ተጋላጭ መሆናቸውንም ተናግረዋል።

እንዲሁም ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች በ72 ሰዓት ውስጥ ወደ ጤና ተቋም አለመምጣት በሽታውን ቅድሚያ ለመከላከል መድኃኒቶች እንዳያገኙ በማድረጉ ተጋላጭነትን ለመቀነስ አዳጋች አድርጎታል ብለዋል።

ዶክተር ጉሻ በክልሉ የመድኃኒት አቅርቦት የተወሰነ መቆራረጥ ቢኖርም በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ያሉ ሲሆን፤ በማህበረሰቡ ዘንድ በሽታው የለም የሚል እሳቤ የተሳሳተ መሆኑን ተረድቶ እራሱን ከበሽታው መከላከል ይኖርበታል ብለዋል፡፡

ቢሮው ስለበሽታው አስጊነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ከመስጠት ባለፈ የምክር አገልግሎት፣ የምርመራ



እንዲሁም በሽታው በደማቸው ላሉ የመድኃኒት አገልግሎት አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል፡፡

ዶክተር ጉሻ ቢሮው ኤች.አይ.ቪን በ2030 የማህበረሰብ አደጋ የማይሆንበት ደረጃ ላይ ለማድረስ እንደሚሠራም አስታውቀዋል፡፡



ዶክተር ለሚ ኮርሶ

# በባቱ ከተማ ከበጋ መስኖ ስንዴ 147 ሺህ 350 ኩንታል ይጠበቃል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>ባቱ</u>፡- በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን በባቱ ከተማ በዘንድሮ ዓመት በጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከ147 ሺህ 350 ኩንታል በላይ ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ የከተማው ግብርና ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

የባቱ ከተማ ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ ዶክተር ለሚ ኮርሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በከተማው 4 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ ከ4 ሺህ 200 ሄክታር በላይ መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል። በዚህም 4 ሺህ 652 አርሶ አደሮች በኩታ ገጠም በበጋ መስኖ ልማቱ እየተሳተፉ ሲሆን ከዚህም 147 ሺህ 350 ኩንታል ምርት ይጠበቃል።

ዕቅዱን ስኬታማ ለማድረግ ምርትና ምርታማነትን በሚያሳድጉ ግብዓቶች አጠቃቀም፣ አዘገጃጀትና በመስመር መዝራት ዙሪያ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች ለአርሶ አደሩ መሰጠቱን የገለጹት ዶክተር ለሚ፤ ከተማ አስተዳደሩ ከክልል ቢሮ ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር የትራክተር፣ የማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘር፣ የውሃ ፓምፕ፣ የባለሙያ ድጋፍ እንዲሰጥ አድርጓል ብለዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ በተሻለ ሁኔታ በለማባቸው አካባቢዎች ላይ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አርሶ አደሮች ተዘዋውረው እንዲመለከቱ በማድረግ የልምድ ልውውጥ ሥራዎች ሲከናወኑ ነበር ያሉት ዶክተር ለሚ፤ ይህም የአርሶ አደሩን ግንዛቤ በማሳደግ በቀጣይ የተሻለ ምርት ለማልማት ይረዳል ብለዋል፡፡

በከተማው ያሉትን የውሃ አማራጮች አርሶ አደሩ በተቻለው መጠን እንዲጠቀምባቸው እና ስንዴ በበጋ መስኖ እንዲለማ በማድረግ በኅብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ መነቃቃት እንደተፈጠረ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ለሚ ገለጻ፤ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ምርታማነትን ከማሳደግና ድህነትን ከመቅረፍ አንጻር ሚናው ጉልህ ነው። በመሆኑም የህልውና ጉዳይ የሆነው የስንዴ ምርትን በማምረት ከውጭ የሚገባውን ምርት በሀገር ውስጥ ለመተካት ይሠራል።

እንደ ሀገር የምግብ ዋስትና በአስተማማኝ መልኩ ማረጋገጥ የሚቻለው የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማት ሲጨምር መሆኑን አስረድተው፤ የባቱ ከተማ ግብርና ጽህፈት ቤት የከተማዋን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ጠንካራ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

# ከተማ አስተዳደሩ የኩላሊት እጥበትን ተደራሽ ለማድረግ እየሠራ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ከተማ አስተዳደሩ የኩላሊት እጥበትን በነባርና እየተገነቡ ባሉ ተቋማት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በልዩ ትኩረት እየሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ አስታወቀ።

በዳግማዊ ምኒልክ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተቋርጦ የነበረው የኩላሊት እጥበት ሥራ ጀምሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ በሆፒታሉ ተገኝተው እንደገለጹት፤የኩላሊት እጥበትን በነባርና እየተገነቡ ባሉ ተቋማት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ከተማ አስተዳደሩ በልዩ ትኩረት እየሠራ ነው።

በሆስፒታል ተቋርጦ የነበረው የኩላሊት እጥበት ዳግም ሥራ የጀመረ ሲሆን፤ ቀድሞ በሆስፒታሉ በነበሩ 4 ማሽኖችና ከሜድሮክ ኢትዮጵያ በተገኘ ድጋፍ 10 አዳዲስ ማሽኖች በድምሩ በ14 ማሽኖች ታግዞ አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል።

በኩላሊት እጥበት ላይ ያሉ የግብዓት እጥረቶችን ለማስወገድ በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል፣በአዲስ አበባ ጤና ቢሮና የአብ ሜዲካል ሴንተር መካከል



ዶክተር ዮሐንስ ጫላ፤

የሦስትዮሽ ስምምነት ተደርጎ ሲሠራ እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር ዮሐንስ፤ የአብ ሜዲካል ሴንተር በስምምነቱ መሠረት ግዴታውን በአግባቡ ባለመወጣቱ አገልግሎቱ ተቋርጦ እንደነበር ተናግረዋል።

ዶክተር ዮሐንስ አክለውም፤ ከኩላሊት እጥበት ጋር ተያይዞ ያለው አገልግሎት ቀልጣፋ እንዲሆን ግብዓት ከሚያቀርቡ ድርጅቶች ጋር በመዋዋል እንዲቀጥል ይደረጋል ብለዋል።

በተለይ የማስፋፊያ ቦታዎችን ከመገንባት አኳያ ከተማ አስተዳደሩ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

ለአብነትም በንፋስ ስልክና ኮልፌ ክፍለ ከተሞች ሁለት ትልልቅ ሆስፒታሎች ተገንብተው በመጠናቀቅ ላይ ናቸው ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ሆስፒታሎቹ እያንዳንዳቸው ከ450 በላይ አልጋ የሚይዙና ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ናቸው ብለዋል።

በተጨማሪም በነባር ሆስፒታሎች ላይ ትልልቅ ግንባታዎች መኖራቸውንና ከነዚህም መካከል የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል፣ ጥሩነሽ ቤጂንግና ራስ ደስታ ሆስፒታል ተጠቃሽ መሆናቸውን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለጻ፤ ከተማ አስተዳደሩ በተደራሽነት ላይ ችግር የለበትም፤ ነገር ግን ከፍትሐዊነትና ከአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ጋር ተያይዞ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት ትኩረት ተደርጓል።

የኩላሊት ሕመምን በሚፈለገው ልክ ለመቀነስ መከላከል ላይ ያተኮረ የኅብረተሰቡ ግንዛቤ ሊኖር እንደሚገባም ዶክተር ዮሐንስ ምክረ ሃሳብ ሰጥተዋል።

# የግብርና ዘርፉን በማዘመን የሥርዓተ ምግብ ሽግግርን እውን ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ዘላለም ግዛው**

**<u>አዲስ አበባ</u>**፡- የግብርና ዘርፉን በዲጂታል ላይ የተመሰረተ እና የማምረት ሂደቱን የማዘመን ትግበራዎችን በማጠናከር ለሥርዓተ ምግብ ሽግግር የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ገለጸ፡፡

የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ማንደፍሮ ንጉሴ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዲጂታል ሥራውን የሚያሳድጉ በርካታ የፍኖተ ካርታ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው፡፡

ፍኖተ ካርታዎቹ ወደ ትግበራ እየተቀየሩ፣ በተለይ በአይቲ የተመረቁ ወጣቶችን በማሰልጠን መተግበሪያዎችን እየሠሩ ወደ እርሻ ሥራ እንዲገቡ እና ዘርፉ የሥራ እድል እንዲፈጥር ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

ኢንስቲትዩቱ የትራንስፎርሜሽን ተቋም እንደመሆኑ የግብርና ዘርፉን የሚያሸጋግር ጥናት በማካሄድ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ ከተመሰረተባቸው ምሰሶዎች መካከል እንደሚጠቀስም ጠቁመዋል፡፡

የቀረበው ሃሳብ ወደ ትግበራ እንዲሸጋገር ለተቋማት ድጋፍና አቅም ግንባታ መስጠት፣ ለአዳዲስ የፈጠራ ሥራዎች የሠርቶ ማሳያ መሥራትና የማስተሳሰርና የማስተባበር ሥራ ትግበራም ኃላፊነት እንደተጣለበትም ነው የገለጹት፡፡

ዘርፉ በዲጂታል ላይ እንዲመሰረት እየተደረገ ነው፤ የግብርናውን ዘርፍ የማምረት ሂደት ዘመናዊ የማድረጉም ሂደት በትኩረት ይሠራል፤ ትግበራዎቹም ለሥርዓተ ምግብ ሽግግር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ብለዋል ዶክተር ማንደፍሮ፡፡

95 ሺህ የሚሆኑ አርሶ አደሮች በክላስተር ተደራጅተው እንዲያርሱ መደረጉን በመጠቆም፤ በክላስተር መሰባሰባቸው የምርምር ውጤት እንዲጠቀሙ፣ ግብዓት ቅድሚያ እንዲኖራቸው፣ ያመረቱትን ወደገበያ አንድ ላይ ሰብስበው መሸጥ እንዲችሉ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በግብርናው ዘርፍ ምርታማነት እንዲጨምር እና ገቢያቸው እንዲያድግ በማድረግ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በዚህ መልክ የተደራጁ ስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን አርሶ አደሮች መኖራቸውንም አመልክተዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ አርሶ አደሮቹን በማብቃት በቀጣይ ወደ ኩባንያ የማሳደግ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ አንድ ላይ በማሰባሰብ ዘር ማምረት ላይ እንዲገቡ እውቅና ይሰጣቸዋል፡፡

ለዘር ማምረት የሚያስፈልግ ማከማቻ መጋዘንም ይገነባላቸዋል፡፡ ለዘር ሂደቱ የሚያስፈልገው ማበጠሪያ፣ ማሽኒያና መሰል ግብአቶች አቅርቦት እንዲሁም ያመረቱትን ምርት እውቅና እንዲያገኙ እገዛ እንደሚደረግላቸውም ነው የጠቀሱት፡፡

በየክላስተሩ የተደራጁ አርሶ አደሮች በየወረዳቸው ካሉ 300 ሱቆች በአንድ መስኮት አገልግሎት ዘርም ሆነ ሌሎች አስፈላጊ ግብአቶች እንዲያገኙ እንደሚደረግም አመልክተዋል፡፡

አርሶ አደሮች የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከል ተቋቁሞላቸዋል ያሉት ዶክተር ማንደፍሮ፤ የራሳቸው ትራክተር ይኖራቸዋል፤ ትራክተሮቹ ይከራያሉ፤ ወደ ሜካናይዜሽን እየተሸጋገሩ ይሄዳሉ ብለዋል፡፡

“አርሶ አደሮች ወይንም ተደራጅተው የሚሰሩ ማህበራት ትራክተር መግዛት ቢፈልጉ የማሰልጠን፣ እና እውቅና የመስጠት አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ለማሽኖቹ የሚሆን መለወጫ ያቀርባሉ፡፡ ተሽከርካሪዎቹ ቢበላሹ የጥገና አገልግሎትም እንዲሰጡ እውቀትና ክህሎት እየተደራጀ እንዲሄድ ይደረጋል” ብለዋል፡፡

በዋና የሰብል ወቅትም ሆነ በመስኖ ማልማት እንዲችሉ የከርሰ ምድር ውሃ ያለበትን አካባቢ በመለየት እንዲጠቀሙ የማድረግ ሥራ እንደሚተገበርም ነው የተናገሩት፡፡

የገጠር የኤሌክትሪክ ተደራሽነት አነስተኛ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት በፀሐይ ኃይል የሚሠራ የመስኖ አውታር እየተዘረጋላቸው እንደሆነ ጠቁመው፤ በግለሰብ ደረጃ የሚጠቀሙ በርካታ አርሶ አደሮችንም ማፍራት እንደተቻለ ተናግረዋል። በክላስተር ለሚያመርቱትም በጋራ ዘርግተው በመጠቀም እንዲያመርቱ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

የመሠረተ ልማት ተደራሽነት አንዱ ተግዳሮት ሊሆን ይችላል ያሉት ዶክተር ማንደፍሮ፤ አርሶ አደሮች በክላስተር ተደራጅተው ያመረቱትን ወደ ገበያ ለማውጣት የመንገድ ተደራሽነት እና የማከማቻ መጋዘን አለመኖር በተፈለገው ፍጥነት ለመጓዝ እንቅፋት ይፈጥራሉ ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የግል ባለሀብቶች መጋዘን ገንብተው እንዲያከራዩ የማስተሳሰር ሥራ እየሠራን እንገኛለን ያሉት ዶክተር ማንደፍሮ፤ ለቀጣይ አምስት ዓመታት ሥራዎችን ሊያሠራን የሚችል በጀት አለን ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዓድዋ ድህነትን ለማሸነፍ የመንፈስ ስንቅ ነው!

የዓድዋ ድል ሁሉም ኢትዮጵያውያን በከፍተኛ ተጋድሎና መስዋዕትነት ሀገራችንን ያስከበሩበት ለጥቁር ሕዝቦች ሁሉ አንፀባራቂ የሆነ ድል ነው፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን በጋራ መታገል እና በጋራ ድል መቀዳጀት የካበተ ልምድ ያለን ሕዝቦች መሆናችን የዓድዋ ድል ትልቅ ታሪካዊ ማሳያ ነው። ጀግኖች አባቶች በከፈሉት መስዋዕትነት ድልን አጎናጽፈውናል፤ ለዚህ ክብር ላበቁን አርበኞች ክብር ይገባቸዋል፡፡

ዓድዋ የመላው ኢትዮጵያውያን የአብሮነት፣ የአሸናፊነትና የጽናት ተምሳሌት ነው። የዓድዋ ድል በኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ለሚገጥሙን የውስጥና የውጭ ፈተናዎች ሁሉ መሻገሪያ ድልድይ መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሳየ ታሪካዊ ኩነት ነው።

ኢትዮጵያዊነታችን የጋራ ማንነታችን ምንጭ ነው። ሉዓላዊነታችንና ነፃነታችን በጋራ የከፈልናቸው መስዋዕትነቶች ውጤቶች ሲሆኑ፣ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ባሕል አለመዳበር ደግሞ የጋራ ስብራታችን ነው።

እርስ በርሳቸው ለመታረቅ ተነሳሽነት የሌላቸው "የወዲያ ማዶና የወዲህ ማዶ" ጽንፈኛ የፖለቲካ አቋሞች ለዘመናት ሀገራችንን የጎዱ በመሆናቸው ከስር ከመሠረታቸው መታረም አለባቸው።

ኢትዮጵያ ከድህነት ጋር የምታደርገውን ትንቅንቅ ለአንዴና ለመጨረሻ ለመቋጨት ኢትዮጵያውያን ተፈጥሯዊ ልዩነቶችን እንደፀጋ በመውሰድ ለጋራ ሀገራችን በጋራ በአብሮነት መቆም መቻል አለብን። ኢትዮጵያውያን በጋራ ሲቆሙ እንደ ዓድዋ አስደማሚና ለዓለም ሁሉ ትንግርት የሆኑ ታሪኮችን ማስመዝገብ እንደሚችሉ አስመስክረዋል። ጀግኖች አባት/እናቶቻችን በዓድዋ የጥቁሮች ሁሉ ቀንዲል የሆነ ድልን አስመዝግበው፣ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ሐረር ግንብ፣ አባጅፋርና የጢያ ትክል ድንጋይን የመሳሰሉ ታሪካዊ ዐሻራዎችን በማኖር ኩራትና ምንዳ ጥለው አልፈዋል።

ኢትዮጵያውያን በዚህ ዘመንም የዓባይ ግድብን ጨምሮ ወንጪ፣ ኮይሻ፣ ጎርጎራና ሀላላ ኬላን የመሳሰሉ ሀገራዊ ገፅታን የሚቀይሩ ፕሮጀክቶችንና ዓለምን ያስደመመ አረንጓዴ አሻራን በማሳረፍ በአንድ ስንቆም መበልጸግ እንደምንችል አስመስክረናል። ኢትዮጵያዊያን በኅብር ስንቆም አርበኞች ነን ብለን እንድናምን የሚያደርገንም ይህ ነው! ሁሌም በድል ለመራመድና ሀገራዊ የብልጽግና ጉዞችንን ለማረጋገጥ በኅብር ሀገራዊ ገዥ ትርክት የሆነውን ብሔራዊ አርበኝነት ማጽናት ይገባል።

በጋራ ቆመን የበለፀገች ኢትዮጵያን መገንባት የምንችልበት እርሾ በእጃችን ላይ አለ፡፡ ልዩነቶቻችንን አጥብበን በማያግባቡን ጉዳዮች ላይ በውይይትና ዕርቅ በመፍታት ነባር እሴቶቻንን በማስቀጠል በሀገራዊ ገዥ ትርክታችን በመግባባት ለቀጣዩ ትውልድ የተሻለች ኢትዮጵያን ማሻገር አለብን፡፡

ዓድዋ ጥሎልን ያለፈው ምንዳ አብሮነትን ከዶ ልዩነቶቻችን ላይ ብቻ ማተኮርን አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ እርስ በርስ መፈራረጅ ላይ የተመሠረተውን የኢትዮጵያን የፖለቲካ ባሕል ወደ ትብብር ለማሻገር ሕያው የዓድዋ ድል ብዙ ያስተምረናል፡፡

ኢትዮጵያውያን እልፍ አዕላፍ የወል ማንነቶችና ድሎች ባለቤት ነን። በጋራ በትብብር የምንኖርባት አንዲት ውድ ሀገር ኢትዮጵያ ስላለችን የወል ማንነት ያለን ሕዝቦች ነን። የኢትዮጵያን የፖለቲካ ባሕልና ታሪክ ኢትዮጵያዊ በሆነ ሀገር በቀል መነፅር የቃኘ፣ ላለፈው ትውልድ ወረት እውቅና በመስጠት በዚያው ላይ ለመገንባት የቆረጠ፣ የነበሩትንና ያሉትን የፖለቲካ ተቃርኖዎች ከመሠረታቸው በመፍታት ዘላቂ፣ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግሥት ለመገንባት ቆርጠን መነሳት አለብን።

የዓድዋን ድል ለኅብረብሔራዊ አንድነታችንና ሁለንተናዊ ብልጽግናችን ለማረጋገጥ መጠቀም የዚህ ትውልድ ታሪካዊ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል! እኛም የዛሬ ትውልዶች ለአርበኞቻችን ክብር እየሰጠን ዘመኑን በመዋጀት ከአባቶቻችን ልቀን እንጂ አንሰን እንዳንገኝ የዛሬውን የጋራ ጠላት የሆነውን ድህንትን በማሸነፍ ለቀጣዩ ትውልድ የበለጸገች ኢትዮጵያን የማስረከብ ኃላፊነታችንን መወጣት ይኖርብናል።

የዓድዋን ድል ለኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን መጠቀምና ሁለንተናዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ የዚህ ትውልድ ታሪካዊ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል። እንደ ዓድዋ ድል ሁሉ ኢትዮጵያን ወደላቀ ከፍታ ለመውሰድና ታሪኳና ክብሯን የሚመጥን ሁለንተናዊ ከፍታ ለማብሰር የሁሉንም ኢትዮጵያውያን የጋራ አስተዋፅዖ ስለሚጠይቅ ዘመን ተሻጋሪና አካታች የሆነ ብሔራዊ ገዥ ትርክት በመገንባት ለትውልድ ማውረስ ወሳኝ ነው፡፡

የዓድዋ ድል ስኬታማ የሆነው በመላው ኢትዮጵያውያን የተደመረ የአንድነት መንፈስ በመሆኑ አሁንም ሆነ ወደፊት የሀገራችንን ዕድገትና ብልጽግና የምናረጋግጠው አሰባሳቢ በሆነ ብሔራዊ ገዥ ትርክት የወል እውነቶቻችንን እያፀናን በአብሮነት ዋነኛ ጠላታችን የሆነውን ድህነት ለማሸነፍ በምናደርገው ጉዞ ነው። ለዚህ ደግሞ የዓድዋ ድል ትልቅ የመንፈስ ጥንካሬያችንና ስንቃችን ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተሳትፎ ከእነ ግለቱ እንዲቀጥል

ዘካርያስ

ኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብቷን መሠረት ከግብርና ዘርፍ ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር ራዕይ ሰንቃ ለተግባራዊነቱ መሥራት ከጀመረች በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በእድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ዘመናት የተጀመረውን ይህን እቅድ ተፈጻሚ ለማድረግ በሚያስችሉ ተግባሮች ላይ በስፋት ሠርታለች፤ እየሠራችም ትገኛለች፡፡

ለእዚህም በመንግሥት ደረጃ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ለመሠማራት የተከናወነውን ተግባር በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የስኳር ኢንዱስትሪዎች፣ የማዳበሪያ ፋብሪካ፣ በርካታ የኃይል ማመንጫዎች ላይ ለመሥራት ታቅዶ ወደ ትግበራ መገባቱ ይታወሳል፡፡

ምንም እንኳ የማዳበሪያ ፋብሪካው ጉዳይ የሀገር አንጡራ ሀብት ይዞ ቢጠፋም፣ የስኳር ፋብሪካዎቹም እንደታሰበው ባይሆኑም፣ የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታውም የሆነ ርቀት ተጉዞ ቢቆምም፣ ለእነዚህ ሁሉ ዋና መሠረት እንደሚሆን የሚጠበቀውን የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ በመገንባት በኩል ጥሩ ርቀት መጓዝ ተችሏል፡፡

በኢንዱስትሪው ዘርፍ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈለገውን ያህል መጓዝ ባይቻልም፣ ሀገሪቱ የዘርፉን አስፈላጊነት በማመን በዘርፍ መሥራቷን ግን አጠናክራ ከመቀጠል ውጪ ወደሁዋላ ያለችበት ጊዜ የለም፡፡ እንደ ሀገር የተለያዩ ፈተናዎች ገጥመውም በዘርፉ የመሥራቱ ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ከግብርናው ወደ ኢንዱስትሪ ሽግግር ማድረግ የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ የሚፈጸም ተደርጎ እየተሠራበት ይገኛል። በእዚህም አንዳንድ ለውጦች መታየት መጀመራቸውም እየተገለጸ ነው።

አንዳንድ የግብርናው ዘርፍ ኃላፊዎች እንዳሉትም፤ ግብርናው በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት አሁንም የመሪነቱን ስፍራ ቢይዝም፣ ቀደም ሲል ይይዝ ከነበረው ስፍራ እየቀነሰ መምጣቱን ይገልጻሉ፤ የአገልግሎቱና ኢንዱስትሪው ዘርፎች የግብርናውን ሸክም መቀነስ ጀምረዋል ነው የሚሉት ኃላፊዎቹ፤ ይህም እንደ ሀገር የተያዘው እቅድ ለውጥ ማሳየት መጀመሩን ያመለክታል። የሜካናይዜሽን እየተስፋፋ መምጣትም ሌላው ሲጠቀስ የሚሰማ ነው፡፡

የኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚፈልገውን የመሬት፣ የቴሌኮም፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የመሳሰሉትን መሠረተ ልማቶች ለማሟላት፣ ለዘርፉ የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋ ለማድረግና ለመሳሰሉት ተግባሮች ትኩረት በመስጠት ብዙ ተሠርቷል። ይሁንና ባለሀብቱ ወደ ዘርፉ ሲመጣ እነዚህን ፍላጎቶቹን መመለስ ላይ ግን ችግር ይስተዋል ነበር፡፡ በብዙ ሥራ የመጣን ባለሀብት በአሠራር ችግር ማጣት ወይም ማስደንገጥ ዘርፉን ማድረስ በሚፈለግበት ደረጃ ላይ ለማድረስ አሉታዊ ተፅዕኖ አያሳርፍም ተብሎ አይወሰድም፡፡

መንግሥት ቆይቶም ቢሆን ይህን ችግር ለመፍታት ተንቀሳቀሷል፡፡ እነዚህን አቅርቦቶች በማዘጋጀት በኩል እንደ ሀገር ይታይ የነበረውን ችግር ለመፍታት በተከናወኑ ተግባሮች የሚታዩ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በመገንባት በተለይ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ወደ ሀገሪቱ የሚመጡ ባለሀብቶችን ለማስተናገድ የተከናወነው ተግባር በዘርፉ ከተከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች የሚጠቀሰው ነው ማለት ይቻላል፡፡

በግሉ ዘርፍ ተገንብተዋል የሚባሉትን ሳይጨምር በሀገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተገንብተዋል። የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማቱ በተለይ የውጭ ባለሀብቶች መሬትና መሠረተ ልማት ለማግኘት ወዘተ ይገጥማቸው የነበረውን ችግር ቀንሶታል።

**መንግሥት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ በስፋት ገብተው የሚሠሩበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ይህን ተከትሎም ጥቂት የማይባሉ ባለሀብቶቹ ወደ ፓርኮቹ እየገቡ ናቸው**

የውጭ ባለሀብቶች ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን ጋር ስምምነት ፈጽመው የለማ ሼድ በመረከብ ማሽነሪዎቻቸውን አምጥተው በመትከል በቀጥታ ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታ ፈጥሯል፤ አለበዚያም የለማ መሬት ባለበት በዚህ ስፍራ ገብተው ኢንዱስትሪያቸው የሚፈልገውን አይነት መሠረተ ልማት ገንብተው መሥራት የሚችሉበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች የለማ መሬትና ሼድ ብቻ አይደለም ያላቸው፡፡ እንደ ባንክ፣ ጉሙሩክና የመሳሰሉት ተቋማት ቅርንጫፎችም በዚያ የሚገኙባቸው በመሆናቸው አገልግሎቶችን ፍለጋ ባለሀብቶቹ ሊባክንባቸው የሚችለውን ጊዜና ሀብት የሚያስቀር አሠራር ያላቸውም ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በአገልግሎት አሰጣጥ በኩል ይሰማ የነበረውን ቅሬታም መፍታት አስችሏል፡፡

በእነዚህ መሠረተ ልማቶች በሚገባ በተሟላላቸው ስፍራዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ስመጥር የሆኑ የአልባሳት አምራቾች ገብተው እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነትን ተከትሎ በሀገሪቱ ላይ በተጣለው ማዕቀብ የተነሳ አንዳንዶች ልማቱን በሚፈለገው መልኩ ማስኬድ ባይችሉም አንዳንዶቹ ትተው የወጡበት ሁኔታ ቢኖርም፣ ዛሬም ድረስ ፓርኮቹ በእጅጉ ተፈላጊ ሆነዋል፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፓርኮቹ የውጭ ምንዛሪ ይዘው ለሚመጡና ምርቶቻቸውንም ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ገበያም አቅምም ያላቸውን የውጭ ባለሀብቶች እንዲያስተናግዱ ለማድረግ ነበር የሚሠራው፡ ሀገር ከእነዚህ ባለሀብቶች የምትጠቀመው ይዘው ከሚመጡትና በቀጣይም ከሚያስገኙት የውጭ ምንዛሪ ብቻ አይደለም፡ እውቀታቸው፣ ልምዳቸውና ይዘው የሚመጡት ቴክኖሎጂም እንደ ሀገር የሚፈለግና የኛን የዘርፉን ባለሙያዎች እንዲሁም ባለሀብቶች

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# የኢትዮ - ሶማሊላንድ ስምምነት ስለምን ስጋት ሆኖ ታየ?

**ቃልኪዳን አሳዬ**

ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ፣ በሰላም ማስከበር እንዲሁም ለጂቡቲ የውሃ አቅርቦት በማድረግ ለቀጣናው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትስስር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተች ትገኛለች።

ታዲያ ለቀጣናው ይህን ሁሉ አበርክቶ እያደረገች ሳለ እሷ ከሌላው ስትጠይቅ ለምን የማይቻል ተደርጎ ይወሰዳል? ስለምንስ የኢትዮ-ሶማሊላንድ ስምምነት ስጋት ሆኖ ታየ? ኢትዮጵያ ለቀጣናው ያላት አበርክቶና በዚህ ጉዳይ ዙሪያ የዲፕሎማሲ ሥርዓቱስ ምን መምሰል አለበት? የሚሉት ጉዳዮች ጥያቄ የሚያጭሩ ናቸው።

የአፍሪካ ቀንድ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ጂኦ ፖለቲካ ውስጥ ትልቅ ሚና አለው የሚሉት በዲላ ዩኒቨርሲቲ የታሪክና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች መምህርና ተመራማሪ አብዱ መሐመድ አሊ (ዶ/ር) ናቸው።

በቀጣናው ደግሞ ወሳኝ ድርሻ ያላት ኢትዮጵያ የእርሻ ውጤቶችንና የተለያዩ ግብዓቶችን ለአካባቢው በማቅረብ ላይ ትገኛለች፤ በዚህም ኢትዮጵያ ለቀጣናው ስጋት ሳትሆን ጸጋ መሆኗን የሚገልጹት ተመራማሪው፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደአፍሪካ ቀንድ መግቢያ በርና ለቀጣናው የኢኮኖሚ ምሶሶ በመሆን ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር በማገናኘት ረገድ የሚጫወተው ሚና የማይናቅ ነው ይላሉ፡፡

ዶክተር አብዱ እንደሚያስረዱት፤ ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር ያደረገችው ስምምነት የኢኮኖሚና የፖለቲካ አንድምታው ላቅ ያለ ቢሆንም ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚነሱ ቅሬታዎች ስህተት ናቸው።

ኢትዮጵያን እንደ ስጋት የሚያዩዋት አካላት መፈጠራቸውንና በቀጣናው የራሳቸው ፍላጎት ያላቸው ሁሉ በጉዳዩ ይመለከተናል በማለት የሚያነሱት ቅሬታ የኢትዮጵያን የቀጣናው አበርክቶ ያላገናዘበ ነው ሲሉ ያነሳሉ፡፡

ስምምነቱ ስጋት የሆነበት ምክንያት ከ30 ዓመታት በላይ ያለ ባህር በር የቆየችው ኢትዮጵያ ወደኤደን ባህረ ሰላጤና ቀይ ባህር ወደብ አግኝታ ከገባች የአካባቢው የኢኮኖሚ ማዕከል ከመሆኑዋም በተጨማሪ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዘመናዊ መሳሪያዎችን መታጠቁና ነገ ላይ ባህር ኃይሉም የባህሩ ንጉስ መሆኑ የማይቀር ስለሆነ ነው ይላሉ። ይህ የሚያሰጋቸው የቅርብም የሩቅም ኃይሎች ደግሞ ከየቦታው ተነስተዋል ሲሉ ያስረዳሉ።

እንደ ዶክተር አብዱ ከሆነ፤ ኢትዮጵያ ለ33 ዓመታት የጂቡቲ ወደብ ጥገኛ ነበረች፤ አሁን ይህ የሚቀየር ከሆነ ጂቡቲን ደስ ይላታል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ኤርትራና ሶማሊያ የራሳቸው የባህር በር ያላቸው በመሆኑ ከሲሳዩ መካፈል ቢፈልጉም ኢትዮጵያ የባህር በር አግኝታ በምጣኔ ሀብትና በወታደራዊ ዘርፍ ጠንክር ብላ መገኘቱዋ ደግሞ ስጋት ነው ብሎ እንደሚያስቡ ተመራማሪው ያመላክታሉ፡

ቀጣናውን እንደፈለጉ ማንቀሳቀስ የሚፈልጉ ኃይላት አሁን ኢትዮጵያ ከ120 ሚሊዮን ሕዝብና ጠንካራ ሠራዊት ጋር ወደባህሩ መጠጋቷ ለእነሱ ትልቅ ስጋት ነው የሚሉት ዶክተር አብዱ፤በመሆኑም በአንዳንድ ኃይሎች የተከፈተው ዘመቻ የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ነው።

ኢትዮጵያ የባህር በር መጠቀምና በስፍራው ወታደራዊ የጦር ሰፈር ማግኘቷ በአካባቢው ያለውን ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ሚዛን እንደሚቀይረው ይጠቁማሉ።

ይህ በመሆኑም የሚከፉ ኃይላት በመኖራቸው ለምን ተከፉ ማለት ሳይሆን በማያስከፋቸው መልክ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የቤት ሥራ መሥራት እንዳለበት ይመክራሉ።

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የኤዥያና ፓስፊክ ሀገራት ዋና ዳይሬክተርና ከፍተኛ ተመራማሪ አንተነህ ጌታቸው (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚያስረዱት፤ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነትና አንድነት በማስጠበቅ የቀጣናው የኃይል ማዕከል መሆን ትፈልጋለች፡፡

በቀጣናውም ሆነ በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለኢትዮጵያ የማይተኙ አካላት አሉ፤ ለዚህም በቀጣናውና በዓለም አቀፍ ላይ ያለውን የኃይል አሰላለፍ በመረዳት የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ባስከበረ መልኩ የጂኦ ፖለቲካ ለውጡን እየተከታተሉ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

ዲፕሎማሲ የሚሠራው ከአንድ ሀገር መንግሥት ጋር በሚደረግ ንግግር ብቻ ሳይሆን ከብዙ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና በርካታ ተዋንያን ጋር በመሆኑ ከእነኚህ አካላት ጋር በመደራደርና የተደራጀ የዓለም አቀፍ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ በማከናወን መጥፎ ገጽታዎች ማስቀየር እንደሚገባ ያመላክታሉ።

ይህም በዲፕሎማቶች፣ በመሪዎችና እንደዜጋ በሁሉም የሚሰራ በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ የተጠና የዲፕሎማሲ ሥራ ማስፈለጉ የማያጠያይቅ ነው ባይ ናቸው። ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላትን ዲፕሎማሲ በተጀመረው አግባብ በማጠናከር ተዓማኒነትን መገንባት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

የአረብ ሊግም ሁሌም በህዳሴው ግድብ ስምምነት ወቅት ከኢትዮጵያ በተቃራኒ ቆሞ መግለጫዎችን ሲያወጣ እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር አንተነህ፤ ይህ ግን ከዓላማችን ሊያደናቅፈን የማይችል መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባ ያነሳሉ።

የባህር በር ጉዳይንም በተመሳሳይ መልኩ ማስኬድ እንደሚያስፈልግ አንስተው፤ እንደ ሳውዲ አራቢያና የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ ሀገራት ከኢትዮጵያ ጋር መልካም ግንኙነት ቢኖራቸውም ሶማሊያ የአረብ ሊግ አባል በመሆኑዋ መተዳደሪያ ደንባቸውም ሊያስገድድ ስለሚችል መግለጫውን አብረው ቢያወጡትም ጉዳዩ ገዝፎ ሊታይ እንደማይገባ ነው የሚያስረዱት።

አንተነህ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ የባህር በር ጉዳይ ለኢትዮጵያ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ነው፤ ጉዳዩ የተጀመረ በመሆኑ ጫጫታውን በመፍራት ወደኋላ ማለት ሳይሆን የዲፕሎማሲ ሥራውን በአግባቡ በመሥራት ከጎረቤት ሀገራትና በቀጣናው ካሉ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር በስልታዊ የዲፕሎማሲ ግንኙነትና ሰጥቶ በመቀበል መርህ ማስኬድ ያስፈልጋል፡፡

# በመዲናዋ የተለያዩ ሕዝባዊ ውይይቶች ተካሄዱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች ትናንትና ሕዝባዊ ውይይቶች ተካሄዱ፡፡

“ሕብረ ብሔራዊ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት ለዘላቂ ሰላምና ሁለንተናዊ ብልጽግና” በሚል መሪ ሃሳብ በተካሄዱ መድረኮች የሀገሪቱና የአካባቢው አጠቃላይ የሰላም፣ የልማትና መልካም አስተዳደር እንዲሁም የሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ያለበት ሁኔታ ላይ ውይይት ተደርጓል፡ ፡

በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክፍለ ከተማ በዓድዋ ድል መታሰቢያ በተካሄደው ውይይት የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣ የኦሮሚያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አወሉ አብዲና በብልጽግና ፓርቲ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞገስ ባልቻ ተገኝተዋል፡፡

በወቅቱ አቶ ተመስገን ጥሩነህ፤ ከሕዝብ የተነሱ ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ መፍትሔ እንደሚሰጣቸው አመላክተው፤ ለሀገራዊ አንድነትና መግባባት ሁሉም የበኩሉን ሊ ወጣ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

በኮልፌ ቀራኒዮ ሕዝባዊ የውይይት መድረክ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አረጋ ከበደና በሚኒስትር ማዕረግ የብልጽግና ፓርቲ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሳዳት ነሻ ተገኝተዋል፡፡

አቶ አረጋ ከበደ በመድረኩ ባስተላለፉት መልዕክት፤ በውይይት መድረኮች የሚነሱ የሕዝብ ሃሳቦችን ወስደን የቀጣይ እቅድ አካል በማድረግ በትኩረት እንሠራለን ብለዋል።

መንግሥት ኅብረ ብሔራዊ አንድነትንና ገዥ ትርክቶችን በማጎልበት ለሁለንተናዊ ብልጽግና እንደሚሠራ ገልጸው፤ በሕዝባዊ ውይይቶች የተነሱ ፍላጎቶችና የመልማት ጥያቄዎችን እንደ ግብዓት በመውሰድ በየደረጃው እንደሚፈታ ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ሲካሄድ የውይይት መነሻ ጽሑፍ ያቀረቡት የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር ተስፋዬ በልጅጌ እንዳመለከቱት፤ የኢትዮጵያን እምቅ ሀብትና የመልማት አቅም እውን ለማድረግ መንግሥት አቅሙን አስተባብሮና ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው።

ባለፉት አምስት ዓመታትም ፈተናዎችን በመቋቋም በርካታ የልማት ሥራዎችን ከማከናወን ባለፈ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ክብርና አንድነት ማስጠበቅ መቻሉንም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያውያንን ብዝሃነትና አንድነት የሚያደበዝዙ የተዛቡ ትርክቶች መኖራቸውን አንስተው፤ እነዚህን የማረምና የማስተካከል ሥራዎች በስፋት እየተከናወኑ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በመሆኑም የተሳሳቱና ከፋፋይ ትርክቶችን በማረም የወል ትርክት በመገንባትና ሀገራዊ አንድነትን የማጠናከር ሥራ የሁሉንም ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑን አመላክተዋል።

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መድረክ የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሙስጠፌ መሐመድ እና የአማራ ክልል የብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ ህፈትቤት ኃላፊ አቶ ይርጋ ሲሳይ ተገኝተዋል፡፡

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ እየተካሄደ ባለው ውይይት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል፣ የአማራ ክልል ም/ርዕሰ መስተዳድር አብዱ ሁሴን (ዶ/ር) እና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል፡፡

በተመሳሳይ በየካ ክፍለ ከተማ መድረክ የገንዘብ ሚኒስትር አሕመድ ሺዴ፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ም/ርዕሰ መስተዳድር እንደሻው ጣሰው፣ የአዲስ አበባ ከተማ ም/ከንቲባ ጀንጥራር አባይ እና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ደስታ ሌዳሞ እና የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር ) በተገኙበት ሕዝባዊ ውይይት እየተካሄደ ነው፡፡

እንዲሁም በልደታ ክ/ከተማ እየተካሄደ ባለው ሕዝባዊ ውይይት የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ኡሞድ ኡጁሉ እና የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሰማ ጥሩነህ (ዶ/ር) ተገኝተዋል፡፡

በተለያዩ ክፍለ ከተሞችም በተካሄዱ መድረኮች ኅብረተሰቡ የመሠረተ ልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የኑሮ ውድነትና የተለያዩ ጥያቄዎችን አንስቶ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ ሕዝባዊ ውይይቱ የማኅበረሰቡን መሠረታዊ ጥያቄዎች በመፍታት ሀገራዊ ድሎችን ለማስቀጠል ያለመ መሆኑ ተገልጿል፡፡

# ኢትዮጵያውያን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በግዛት ማስፋፋት ላይ ተሰማርተው ነበር። በተለይም ከመሪዎቻቸው ከእነ ጎበና ዳጬ፣ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስና ራስ ተሰማ ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ድንበር የሚሉትን ለማስከበር በከፍተኛ ወኔ ዘምተዋል ሲሉ በወቅቱ ውስጣዊ ግጭት እንደነበረ አውስተዋል፡፡

ሆኖም ጣሊያኖች ጥቁሮችን የበታች ለማድረግ ይዘው የተነሱትን ርእዮተ ዓለም ለማስተግበር ኢትዮጵያን በቅኝ አገዛዝ ስር ማድረግ አለብን ብለው ሲንቀሳቀሱ፣ ኢትዮጵያውያን ውስጣዊ ጉዳዮቻቸውን በይደር አቆይተው ህብረ ብሔራዊ አንድነትን ፈጥረው ጠላትን ገጥመው ድል ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ ተባባሪ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ የክተት አዋጁ በተላለፈ ጊዜ አዝማሪው፣ ፈረሰኛው፣ እግረኛው፣ ስንቅ አቀባዩ፣ ውሃ ቀጂው እና ጠመንጃ ያነገተው ሁሉ ተሰባስቧል፡፡

በአንድ በኩል ጣሊያን፣ በሌላ በኩል እንግሊዝና ፈረንሳይ ኢትዮጵያን ከበው ነጻነቷን ለመንጠቅ ሞክረዋል፡፡ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የቅኝ ግዛት ወረራውን ለመቋቋም ቢሞክሩም በመጨረሻ በቅኝ ገዢዎች እጅ ወድቀው ሁለተኛ ዜጋ ለመሆን በቅተዋል፡፡ ጣሊያኖች ይህን ታሪክ ኢትዮጵያ ላይ ለመድገም በማናለብኝነት ከፍተኛ ትግል ቢያደርጉም አልተሳካላቸውም፡፡

ኢትዮጵያውያን በዓድዋ ድል ያሳዩት ህብረብሔራዊ አንድነት በድህረ ዓድዋም ተከትሎ መሄድ ሲገባው አልሆነም ያሉት ዶክተር አየለ፤ ዛሬ ድረስ የእርስ በእርስ ጦርነት እየተከሰተ የሚገኘው ህብረ ብሔራዊነትን ባግባቡ በሥራ ላይ ባለማዋላችን ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ታሪክን የግጭት ምንጭ በማድረግ ዘወትር በትናንሽ ነገር ስንፋጭ እንውላለን፡፡ ይህ ነገር መቀየር አለበት ሲሉም ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር) አሳስበዋል፡፡

አክለውም፤ አሁን የሚታየውን መለያየት ለመቀልበስ የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመው፤ ፍትሐዊነትን ለማስፈን አንዱ የሌላውን ማንነት ማክበር አለበት ብለዋል፡፡

ዓድዋ ሀገር ወራሪ በህብረ ብሔራዊ አንድነት የተሸነፈበትና መልከ ብዙ ሕዝባዊ እሴቶች የታዩበት በመሆኑ ልንጠብቀውና ሀገርን ለማሳደግ ልናውለው የሚገባ አርዓያነት ያለው ታሪካዊ ድል መሆኑን አጽንኦት ሊሰጠው እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡

# ኢትዮጵያ ለአህጉሩና ለምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መንግሥታትና በአፍሪካ ኅብረት ሰላም አስከባሪ ኃይል አማካኝነት በሩዋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ላይቤሪያ፣ ሱዳን ዳርፉር፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳንና ሱዳን አዋሳኝ በሆነችው አቢዬ ግዛት የሰላም ማስከበር ተልዕኮውን በአግባቡ ተወጥቷል፤ እየተወጣም ይገኛል ነው ያሉት አምባሳደር ቆንጂት ስነጊዮርጊስ።

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ያበረከተችው አስተዋጽኦ በነጻነት ተምሳሌትነት ተነሳሽነትን በመፍጠር የተገደበ አይደለም ያሉት አምባሳደር ቆንጂት፤ በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ የአፍሪካ ሀገራት ነጻነታቸውን እንዲቀዳጁ የማድረግ ዓላማ የነበረውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረት የመሪነት ሚና ተጫውታለች ብለዋል።

“አፍሪካ ወገቤን ባለች ጊዜ ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ ደርሶ የደገፉ የሉም” ያሉት አምባሳደር ቆንጂት፤ ኢትዮጵያ የሞኖሮቪያ” እና "የካዛብላንካ” ቡድን በሚል ተከፍለው የነበሩትን የአፍሪካ ሀገሮች አዲስ አበባ ላይ በማገናኘትና ልዩነቶችን በማለዘብ ወደ አንድ የጋራ አቋም እንዲመጡ አድርጋለች ብለዋል።

በዚሁ መሰረት ግንቦት 1955 ዓ.ም. ሰላሳ ሁለት መስራች ሀገሮች የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን በይፋ አቋቁመዋል። ለዚህ ድርጅት እውን መሆንም ኢትዮጵያ የመሪነት ሚና መጫወቷንም ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደር ቆንጂት ገለጻ፤ የአፍሪካ ሀገራትን ነጻነት ማረጋገጥ ቀዳሚ ዓላማው አድርጎ የተመሰረተና ዓላማውን ያሳካው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረትና ተልዕኮውን እንዲወጣ በማድረግ ረገድ የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ትልቅ ድርሻ ነበራቸው፡፡

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተልዕኮውን ሲያጠናቅቅ በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኅብረት ተመስርቷል ያሉት አምባሳደር ቆንጂት፤ የአፍሪካ ኅብረት በአዲስ የአፍሪካ ራዕይ እንዲፈጠርና ወደሥራ እንዲገባ በማድረግ ረገድ ኢትዮጵያ ከአራት አስርት ዓመታት በፊት እንዳደረገችው ሁሉ የጎላ ድርሻ ነበራት ብለዋል።

ኢትዮጵያውያንና ቀደምት የሀገሪቱ መሪዎች ለአፍሪካ ነጻነት ያበረከቱትን ታላቅ አስተዋጽኦ አስታውሰው፤ አዲስ የተመሰረተው የአፍሪካ ኅብረት ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ እንዲሆን አድርገዋል ያሉት አምባሳደር ቆንጂት፤ ይህንን ትውልዱ ማስቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ከምርት ጠባቂነት እየወጣ ያለው የጅማ ከተማ ግብርና

**አስቴር ኤልያስ**

የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ እንደሚያሳየው አብዛኛው ዜጋ ከገጠር ወደ ከተማ የሚያደርገው ፍልሰት ከዕለት ወደዕለት እየጨመረ ነው፡፡ ለፍልሰቱ የራሱ የሆነ ገፊ ምክንያት ቢኖረውም የከተማ ነዋሪው ቁጥር ግን ከፍ እያለ ስለመሔዱ አጠራጣሪ አይደለም፡፡ የከተሜው ቁጥር ከማሻቀቡ ጋር ተያይዞ ለኑሮ ውድነቱ ጫና እየፈጠረ ይገኛል፡፡

የከተማ ነዋሪዎችን የድህነት ሁኔታ ለማሻሻል ያግዝ ዘንድ መንግሥት የከተማ ግብርናን እንደ አንድ አማራጭ በመያዝ ወደሥራ ገብቷል፡፡ ይህ የከተማ ግብርና በሁሉም አካባቢ ተግባራዊ መሆን ከቻለ ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት እንዲኖር ከማድረግ ባሻገር የምግብ ዋስትናንም ለማረጋገጥ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ አሁን አሁን በከፍተኛ ሁኔታ ሕዝቡን የተጫነው የኑሮ ውድነት ከመቀነስ አኳያም ሚናው ላቅ ያለ ነው፡፡

ከሰሞኑን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን ወደ ጅማ በማቅናት የጅማ ከተማ ግብርና ጽሕፈት ቤትን መዳረሻው አድርጓል፡፡ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ አብዱላዚዝ ጀማል እንደሚናገሩት፤ የከተማ ግብርና ከዚህ ቀደም ትኩረት አልተሰጠውም ነበር። ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በተለይም ላለፉት ሁለት ዓመታት መንግሥት ለከተማ ግብርና ትልቅ ትኩረት በመስጠት እየሠራ ይገኛል፡፡

የከተማ ግብርና የከተማውንና በዙሪያዋ ያሉ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ከተማው የሚታወቀው በንግድ ማዕከልነቱ ነበር፡፡ የግብርና ምርት የሚያገኘው በዙሪያው ካሉ ቀበሌዎችና አጎራባች ወረዳዎች ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ከተማ የንግድ ማዕከል ብቻ ሳይሆን ተመርቶ የሚሸጥበትም ሆኗል፡፡ በተለይም ከለውጡ በኋላ መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እያንዳንዱ ከተማ የራሱን ምርት ለማምረት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ዘንድሮ እንደ ሀገር፣ እንደክልልም ሆነ እንደከተማም አስተዳደር ሰፊ እቅድ የታቀደ ሲሆን፣ ያንን እቅድ ለማከናወን ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በጥምረት በመሥራት ላይ ነው፡፡ እቅዱ ተግባራዊ እንዲሆን የከተማ ነዋሪውና በከተማው የታቀፉ በከተማው ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮችም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

በዚህ ረገድ እኛም እንደ ግብርና ጽሕፈት ቤት ባለሙያዎቻችን በማደራጀት አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ ቅስቀሳ አድርገን አጠናክረናል የሚሉት አቶ አብዱላዚዝ፣ በጅማ ከተማ አስተዳደር የሚተዳደሩ 17 ቀበሌዎች እንዳሉም ይናገራሉ። በእነዚህ ቀበሌዎች ውስጥ ያሉ የከተማ ነዋሪዎችና አርሶ አደሮች ሙያዊ ድጋፍ አግኝተው እንዲሠማሩ ማድረጋቸውን ይጠቅሳሉ። የቀበሌዎቹ ነዋሪዎች በግብርና ሥራ እንዲሳተፉ ከፍተኛ ቅስቀሳ ተደርጎ በመሥራት ላይ መሆናቸውንም ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ በዚህ ዙሪያ ዘንድሮ ልዩ እቅድ ተደርጎ እየተሠራ ነው፡፡ ከተማ ሰፊ ሕዝብ፣ አነስተኛ መሬት ያለው እንደመሆኑ፤ አነስተኛ መሬት ምርታማ ይሆን ዘንድ ቴክኖሎጂን መጠቀም የግድ የሚል ነው፡፡ ይህን በማድረግ ጠባቂነቱን በመተው ለራሱ ብቁ መሆን እንዲችል እየተሠራ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር እንደ ጅማ ከተማ ሰፋፊ መሬት ያላቸው አራት ቀበሌዎች አሉ፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች በፊት የከተማ ግብርና ትኩረት ባላገኘበት ጊዜ ሙያዊ ድጋፍ አያገኙም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ሁሉንም የግብርና ግብዓት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በገጠር ያሉትም ባላቸው ሰፋ ያለ መሬት፣ በከተማ ያሉ ባላቸው አነስተኛ መሬት ጓሯቸውንም ሆነ ግድግዳቸውንም ተጠቅመው "ምግቤን ከጓሮዬ" በሚለው መርሕ እንዲያመርቱ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ‹‹በእርግጥ ይህ ተነሳሽነት በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር በአቅጣጫ መልክ የተቀመጠው አምና ሲሆን፣ እኛም እንደ ከተማችን አቅጣጫውን




**አቶ አብዱሳዚዝ ጀማል**

በመቀበል ወደተግባር የመቀየር እንቅስቃሴ ጀምረናል›› ይላሉ፡፡ በተለይ ሰፋፊ መሬት ያላቸው በመስኖም ሆነ በክረምቱ ወቅት እንዲያመርቱና ለራሳቸውም ለገበያም በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሠራ መሆኑንም ይናገራሉ፡፡

በከተማ ግብርና የሚሠራው በጋ ላይ በመስኖ፤ ክረምት ላይ በዝናብ ማምረት ብቻ ሳይሆን በእንስሳት ማርባት ዙሪያም ጭምር ነው፡፡ በከብት፣ በዶሮና በንብ ማነብ ላይ የተለያዩ ሥራ አጥ ወጣቶችም በመሳተፋቸው የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን ይጠቅሳሉ፡፡ እንደ ጅማ ከተማ አስተዳደር ሰፊ ሥራ መሠራቱን ኃላፊው ይናገራሉ። ሼዶችን በክላስተር በመሥራት ለተደራጁ ሥራ አጥ ወጣቶች እንዲጠቀሙበት ተደርጓል፡፡

ለአብነት ለዶሮ፣ ወተት ከብት እርባታ፣ ለከብት ማድለብ እና ለንብ ማነብ ሥራ ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ በመመደብ ሼዶች ተገንብተዋል፡፡ ከተማ አስተዳደሩ በራሱ በጀት ከሚሠራው ሥራ አልፎ ግንባር ቀደም አርሶ አደሮች፣ ማኅበራትና ባለሀብቶች በዚህ ሥራ ገብተው አምርተው የከተማውን ማኅበረሰብ ፍላጎት እንዲያሟሉ ሰፊ ሥራ ተሠርቷል፡፡

እንደኃላፊው ማብራሪያ፤ የከተማው ግብርና ሥራ የከተማውንና በከተማው ዙሪያ ያሉ ቀበሌዎችን የወተት፣ ዶሮና እንቁላል ፍላጎት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በማሟላት ላይ ነው፡፡ ለሥራ አጥ ወጣቶችም የሥራ እድል በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡ ሌላው በከተማ ግብርና ከሚሠራው ውስጥ ተጠቃሹ ንብ ማነብ ነው። ቀደም ሲል የማር ምርት ለከተማው ነዋሪ ይመጣ የነበረው ከገጠር ቀበሌዎች ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ግን በከተማ ውስጥም ንብ ማነብ ይቻላል የሚለውን መርሕ በመከተል ማምረት ተጀምሯል፡፡

በጅማ አካባቢ በዓመት ሦስት ጊዜ አበባ ሊሆኑ የሚችሉ ዛፎች በመኖራቸው ለማር ማምረት ምቹ ሁኔታ መኖሩንም ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም ራሳቸው አምራቾቹም ሆኑ የከተማው ነዋሪ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ ሰፊ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ከተወሰኑ ወራት በኋላ ማር የሚቆርጡ ወጣቶች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ በቀጣይ ደግሞ በዘርፉ በመደራጀት ላይ ያሉ ወጣቶች እንዳሉም ተናግረዋል፡፡

‹‹በሁሉም ዘርፎች ሙያዊ ድጋፍ በሚያስፈልግበት ሰዓት ቀን ከሌት በመሥራት ላይ እንገኛለን›› የሚሉት አቶ አብዱላዚዝ፣ ለአብነት ያህል ንብ ወደቀፎው የሚገባው ምሽት ላይ በመሆኑ ባለሙያዎቹ በቦታው ተገኝተው ሙያዊ ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው ይናገራሉ፡፡ በዶሮና በከብቶቹም ዙሪያ ከእርባታ ሒደታቸውና ጤናቸውን ከመጠበቅ አኳያ እንዲሁ ሙያዊ ድጋፋቸው እንደማይለይ ያስረዳሉ፡፡

የከተማው ማኅበረሰብ ከአጎራባች ቀበሌና ወረዳ የግብርና ምርት ከመጠበቅ አልፎ የራሱን ምግብ ራሱ እንዲያመርት በሰፊው እየተበረታታ ይገኛል፡፡ ራሱም ተጠቃሚ ሆኖ ለገበያም እንዲያቀርብ በመሥራት ላይ ነው፡፡ ግብርና ጽሕፈት ቤት- ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመሆን ያልተቋረጠ ሙያዊ ድጋፍ በመስጠትም እየሠሩ ነው፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ በከተማዋ ዙሪያ ባሉ የእርሻ መሬት ላይ የመስኖ ሥራ ይሠራል፡፡ ለምሳሌ ጅማ ከተማን አቋርጠው የሚሔዱ በዙሪያው የሚያልፉ ወንዞች አሉ። 12 ኪሎ ሜትር አካባቢ በሚሆን ርዝማኔ ከተማዋን አቋርጦ የሚሔደው የአዌይቱ ወንዝ ለከተማዋ ውበት ከመሆን ባሻገር ብዙ ቀበሌዎች ላይ የግብርና ልማቱን የሚያሳልጥ ነው፡፡ በየቀበሌዎቹ ቲማቲም፣ ጎመን፣ ፓፓያ፣ ሙዝ፣ አናናስና ሌሎቹም ፍራፍሬዎችና የጓሮ አትክልቶች ይመረትባቸዋል፡፡ ሌላው ኪቶ የሚባል ወንዝ ሲሆን፣ አርሶ አደሩ በወንዙ እንዲጠቀም ሙያዊ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ በዚህም ራሱን በመጥቀም ለከተማው ነዋሪም ምርት በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት በኦሮሚያ ግብርና ጽሕፈት ቤትና በኦሮሚያ ከተማ ልማት በጥምረት ለዶሮ እርባታ 300 ሼዶችን ለመሥራት አቅደዋል፡፡ እነዚህን ሼዶች የከተማ አስተዳደሩ፣ ባለሀብቱ እንዲሁም ማኅበራቱ የሚሠሯቸው ሲሆን በአሁኑ ወቅት 194 ሼዶች ተሠርተዋል፤ ከእነሱም መካከል 115 የሚሆኑቱ ሥራ የጀመሩ ናቸው፡፡

የወተት ላሞችን በተመለከተ 100 ሼዶች እንዲሠሩ ታቅዶ በእስካሁኑ ሒደት 82 ሼዶች ተሠርተው 50ዎቹ ወደሥራ መግባት ችለዋል፡፡ የንብ እርባታን በተመለከተ ደግሞ 50 ሼዶችን በማቀድ አምስት ሺ የማር ቀፎዎችን ለማስገባት የታሰበ ሲሆን፣ እስካሁን ወደ 22 የሚሆኑ የተጠናቀቁ ሲሆን 45 ያህሉ ደግሞ ግንባታ ውስጥ ይገኛሉ። ይህም ከእቅድ በላይ ከፍ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የሚያመላክት ነው ባይ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ውስጥም 18ቱ ወደ ሥራ መግባታቸውን ጠቅሰው፤ በዙሪያው ካሉ አርሶ አደሮች ጭምር እስካሁን ወደ ሁለት ሺ 400 የሚሆን የማር ቀፎ በመግባቱ ወደማር ቆረጣው የገቡ አሉ፤ በዚህ አያያዝ ከአምስት ሺ በላይ የማር ቀፎ ማድረስ እንደሚቻልም ግንዛቤ ተይዞበታል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

ኃላፊው እንደሚሉት፤ በዶሮዎች በኩል ታቅዶ የነበረው አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶሮ ለማስገባት ነበር፤ ከዚህ ውስጥ ከስድስት ሺ በላይ ዶሮ ቤት ለቤትም ሆነ በሼዶቹ በማስገባታቸው በአሁኑ ወቅት እንቁላል መጣል የጀመሩ መኖራቸውን ያመለክታሉ። ከዚህ የተነሳ በቅርቡ በጅማ ከተማ በቂ የእንቁላል ምርት ከመኖር ባለፈ ለሌላም አካባቢ የሚተርፍ እንዲሆን አቅደው እየሠሩ ይገኛል፡፡

አቶ አብዱላዚዝ እንደሚሉት፤ የከተማ ግብርናን ለማሳለጥ ጅማ ምቹ ናት፡፡ የትኛውም ቤት ያለው የከተማዋ ነዋሪ፣ ምግቡን ከደጁ ለማግኘት የሚጠበቅበት ተነሳሽነት ብቻ ነው፡፡ ቦታ እንኳን ባይኖረው በሃይላንድ፣ በተለያየ እቃና በአጥሩ ላይ ጭምር ጎመን፣ ካሮት፣ ቀይ ስርና ሌላውንም የጓሮ አትክልት ማልማትና መጠቀም ይችላል፡፡ ይህ የኑሮ ውድነቱን ከመቀነስ አኳያ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

በቅርቡ ወደከተማ አስተዳደሩ የታቀፉ የተወሰነ መሬት ያላቸው አርሶ አደሮች መኖራቸውን የሚናገሩት አቶ አብዱላዚዝ፣ ለእነዚህ ቀበሌዎች የከተማ ግብርናው የበለጠ ምቹ መሆኑን ያስታውቃሉ። ‹‹የከተማ ግብርና አንዱ ጥሩነቱ ገበያ ፍለጋ ችግር አለመኖሩ ነው፡፡ ስለዚህ በትንሽ ቦታ ላይ ማምረት የሚያስችል ከመሆኑ በተጨማሪ ገበያ ፍለጋም ሩቅ አለመሄዱ ተመራጭ ያደርገዋል›› ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ከጠቀሜታው አኳያ ሲመዘንም ለመሥራት ተነሳሽነት ያለው ነዋሪው ለአትክልትና ፍራፍሬም ገበያ መሄድ አይጠበቅበትም ይላሉ፡፡ በከተማ ግብርና ለመጠቀም የእርሻ ትራክተር ወይም በሬ መጥመድ አይጠበቅብንም የሚሉት አቶ አብዱላዚዝ፣ በቀላል መሣሪያ አምርቶ መጠቀም እንደሚቻል ይጠቅሳሉ፡፡

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ከተጠቃሚነትና ከዋጋ አንጻር ሲታይ ፍላጎትና አቅርቦት ካልተጣጣመ የገበያ መናር ይከሰታልና ሁለቱን ማጣጣም ያስፈልጋል፡፡ ይሁንና በአሁኑ ወቅት እየተሠራ ባለው የከተማ ግብርና አቅርቦትና ፍላጎት ስለሚጣጣም ገበያው ይረጋጋል ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡ ለአብነት የዶሮም፣ የወተት ላሞችንም እርባታ መውሰድ ቢቻል የሁለቱም መኖ በጣም ውድ ነው፡፡ አንድ ኩንታል የዶሮ መኖ ከአራት ሺ ብር በላይ ነው፡፡ አንድ ኩንታል የከብቶች ፉርሽካም ከሁለት ሺ ብር በላይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የግብርና ምርት ይረክሳል ለማለት ይቸግራል፡፡

‹‹ሆኖም ሰው እንቁላልና ዶሮ አሊያም ወተት ፍለጋ ትራንስፖርት አውጥቶ አይሔድም፤ ከዚህ አንጻር በተወሰነ መልኩ ቅናሽ ያሳያል ማለት ይቻላል›› ይላሉ። ከዚህ ጎን ለጎን ሰው ዶሮን አርዶ ለመብላት የበዓላት ቀንን መጠበቅ አቁሟል፡፡ ምክንያቱም በየሰው ቤት ቢያንስ አስርና አስራ አምስት ዶሮ እንዲረባ በመደረግ ላይ ነውና ሲሉ ኃላፊው ይናገራሉ፡፡

ከዚህ አንጻር በመንግሥት በተሰጠ አቅጣጫ የሌማት ትሩፋት በ2015 በጀት ዓመት ተግባራዊ ሆኗል። እንደ ጅማ ከተማ የተሰጠውን አቅጣጫ በመተግበር ላይ ነን ሲሉ ኃላፊው ያመለክታሉ። ነዋሪው ወተቱን፣ ሥጋውን፣ ማሩን፣ አትክልቱን እንዲያገኝ በማድረግ የሌማት ትሩፋት ተጠቃሚ እንዲሆን እየሠሩ መሆናቸውንም ያስረዳሉ፡፡

እንዲያም ሆኖ የከተማ ግብርና ትኩረት የሚሻው ነገር እንዳለው አቶ አብዱላዚዝ አልሸሸጉም፡፡ እንደ ዞንና ወረዳ ሁኔታዎች የተመቻቹ አይደሉም። የኤክስቴንሽን ሥርዓቱ ተጠንቶ እንዳልተዘረጋም ይጠቁማሉ፡፡ በእርሳቸው እይታ የኤክስቴንሽን ሥርዓቱ እንደከተማ ሊዘረጋ ይገባዋል፡፡ የከተማ መሬት በጣም አነስተኛ እንደመሆኑ በቴክኖሎጂ ተደግፎ ብዙ ምርት እንዲሰጥ ማድረግ ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የኤክስቴንሽን ሥርዓቱ በትንሽ መሬት ላይ መሥራት የሚያስችል እንዲሆን ተደርጎ መዘርጋት እንዳለበት ይጠቅሳሉ፡፡ በተጨማሪም ሙያዊ ድጋፍ አሰጣጡ የገጠርና የከተማ አሠራሩ በራሱ ለየቅል በመሆኑ በዚህ ላይም ሊታሰብበት ይገባል ይላሉ፡፡

በመሆኑም የኤክስቴንሽን ሥርዓቱ ተጠንቶ መዘርጋት፣ የከተማ ግብርናን በፖሊሲ መደገፍና የጽሕፈት ቤቱ አደረጃጀትም ምቹና አስፈላጊዎቹን ባለሙያዎች ያሟላ ሆኖ መደራጀት ይጠበቅበታል ሲሉ ያመለክታሉ፡፡ እስካሁኑ እየተሠራ ያለው በነባሩ አደረጃጀት በመሆኑ በዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡ በተጨማሪም ሠርቶ ማሳያዎችና በጀት እንዲሁም በሎጀስቲክም የከተማን ግብርና መደገፍ የሚያስፈልግ ነው፡፡ ሁሉን ነገር ከተማ አስተዳደሩ ሊወጣው አይችልም፡፡ ስለዚህም የከተማ ግብርና በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ለውጥ እያመጣ ያለ ስለሆነ ሥራው መንግሥትን ጨምሮ የተለያዩ የባለድርሻ አካላትን ድጋፍ ይሻል፡፡ ይህ ሲሆን ከፍተኛ ለውጥ እንደሚመጣና ነዋሪውንም ሆነ ሀገርን ይጠቅማል ይላሉ፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የጉባኤው ውሳኔና የአፍሪካ ትምህርት የወደፊት አቅጣጫ

ግርማ መንግሥቴ

ከሁለት ሳምንት በፊት "ትምህርት በአፍሪካ" በሚል ርዕስ አንድ ዳሳሽ ጽሑፍ አቅርበን እንደነበር ይታወሳል። በጽሑፉም በአህጉረ አፍሪካ ትምህርት ያለበትን ሁኔታና ይዞታ፣ በወፍ በረርም ቢሆን ዳስሰናል። ያሉበትን ችግሮች ቃኝተን፤ ከምሑራን ጥናት ተነስተን መፍትሔውን ጠቁመናል፤ መደረግ ያለበትን ከሌለበት ለይተን አሳይተናል።

ይህን ያደረግነውና የአፍሪካ አሕጉርን ትምህርት የኋላ ታሪክ የገመገመውን የዘንድሮው 37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ዐቢይ የመወያያ አጀንዳ ይህንኑ የአፍሪካን ትምህርት የወደ ፊት አቅጣጫ ያስቀመጠ በመሆኑ ነው።

ዛሬም፣ ከጉባኤው መጠናቀቅና ካስተላለፈው ውሳኔ አኳያ አንዳንድ ሀሳብ ለመለዋወጥ በመሻት ጉዳዩን ወደዚሁ ገጽ እንደገና ይዘነው መጥተናል።

የዘንድሮው የኅብረቱ ጉባኤ መሪ ቃሉ "Educate an African fit for the 21st Century: Building Resilient Education Systems for Increased Access to Inclusive, Lifelong, Quality, and Relevant Learning in Africa". የሚል ነው፡፡ በእኛ ትርጉም "21ኛውን ክፍለ ዘመን ያገናዘበና ለአፍሪካ የሚስማማ ማስተማር፤ አይበገሬ የትምህርት ሥርዓት መገንባት ለአካታችነት፣ ጥራት፣ እና ተገቢነት በአፍሪካ እንደማለት ነው።

ይህ መሪ ቃል በአጀንዳ 2063 ለማሳካት ከተያዙት እቅዶች አንዱ ሲሆን፣ እሱም "በአካታች እድገትና ቀጣይነት ያለው ልማትን መሠረት ያደረገ የበለፀገ አፍሪካ" የሚለውና አፍሪካን ለመለወጥና ወደ ብልፅግና ለማምጣት ትምህርት ላይ በከፍተኛ ደረጃ መዋዕለ ንዋይን በማፍሰስ፤ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትን ለአፍሪካውያን በተለይም ለወጣቱ ተደራሽ በማድረግ ወዘተ፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራትን፤ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ አብዮት ማቀጣጠልን፤ ከዛም አፍሪካን ወደ ብልፅግና ጉዞን ማስቀጠልን ታሳቢ ያደረገ ነው።

በአጀንዳው መግቢያና አንዳንድ ገፆችም ሆነ ሌሎች ሰነዶች ላይ እንደሰፈረው፣ በአፍሪካ እንደ ሌሎቹ ሁሉ የትምህርቱ ሴክተርም በተግዳሮት የተሞላ ነው። በደል እየደረሰባቸው ካሉት ዘርፎች ቀዳሚው እንኳን ባይሆን፣ ከፊት መሪዎቹ ውስጥ አንዱ ነው - ትምህርት።

እ.ኤ.አ በመጋቢት ወር 2024፣ "ሴቭ ዘ ችልድረን "EDUCATION IN AFRICA: VIOLENT ATTACKS AGAINST SCHOOLS ROSE 20% IN 2023 በሚል ርዕስ በተጠና ጥናት በአፍሪካ በሚደረጉ የእርስ በእርስ ግጭቶች ምክንያት፣ በተጠናቀቀው 2023 ብቻ ካሉት አጠቃላይ ትምህርት ቤቶች መካከል 20 በመቶ ያህሉ በደረሰባቸው ከፍተኛ ጉዳት ምክንያት ወድመዋል።

ይህ፣ በ411 የመስክ እና ጥናታዊ ሪፖርቶች የተገለፀው አደጋ በትምህርት ሴክተሩ ላይ ትልቅ ጉዳትን ያደረሰ ሲሆን፤ የመማር-ማስተማሩን ሥራ በመግታት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ልጆች ከትምህርት ገበታቸው ውጪ አድርጓል። ስለዚህ ይህ ይቆም ዘንድ አስቸኳይ እርማትን ይፈልጋል ማለት ነው፡፡

ጥናቱ የመሪዎቹ ውሳኔ በትምህርቱ ዘርፍ ያለውን ማነቆ በአፍሪካ አንድ አራተኛ የመጀመሪያ ደረጃ፤ ከሁለተኛ ደረጃ ደግሞ 50 በመቶ ብቻ ናቸው በሙያው የሠለጠኑ መምህራን፡፡ ስለሆነም በመምህራን፣ በተማሪዎች፣ በትምህርት ቤቶች እና ተያያዥ ወገኖች ላይ እየደረሱ ያሉትን ችግሮች ይፈታል፤ የመማር-ማስተማር መሰናክሎቹንም ያስወግዳል ተብሎ ይጠበቃል።

መሪዎቹንም ቃልና ውሳኔያቸውን ወደ ተግባር እንዲቀይሩ፤ የትምህርት ተቋማትንም ለልጆች ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን በጥብቅ ያሳስባል።

በዚሁ የካቲት 9 እና 10/2016 ዓ.ም የተካሄደውን 37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ አስታኮ ይፋ በተደረገው የሴቭ ዘ ችልድረን ጥናት ላይ ልዩ ትኩረትን ካገኙት መካከል በሕፃናት ጉዳይ ላይ ሁሉም አካል እጅ ለእጅ ተያይዞ ይህችን ዓለም ለልጆች ምቹ ማድረግ የሚገባ መሆኑን የሚያስገነዝበው ክፍል ነው፡፡

በዚሁ ክፍል በትምህርት ቤቶች ላይ የጦር መሣሪያ መተኮስ፤ መምህራንን መግደልና ማሰቃየት፤ በተማሪዎች ላይ አስለቃሽ ጋዝ መርጨት እና የመሳሰሉት ባስቸኳይ ቆመው ተማሪዎች ወደ መደበኛ ትምህርት ገበታቸው ተመልሰው፤ መምህራንም ሠላምና ደህንነታቸው ተጠብቆ የመማር ማስተማሩ ተግባር መቀጠል እንደሚገባው ተጠቅሷል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዓለም አቀፍ ተቋማትና የእርዳታ ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ ሊያደርጉ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡



በትምህርት ቤቶች ላይ የአየር ድብደባ መፈፀም፣ የትምህርት ቤቶችን ጥበቃ ኃይላት መግደልና ማሰር፤ የትምህርት ተቋማትን ለወታደራዊ ማሠልጠኛነት መጠቀም ወዘተ በአስቸኳይ መቆም ያለበት መሆኑን የሚገልፀው ይህ ጥናት፤ ችግሩ በመቆም ፋንታ በየዓመቱ እየጨመረ የመሄዱን ጉዳይ "alarming rise in attacks year-on-year ሲል የገለፀው ሲሆን፣ የአሕጉሪቱ መሪዎች ይህንን ችግር ለመፍታት ሲረባረቡ አለመታየታቸውን፤ እንዲሁም የየሀገራቱን የተቀናጀ የፖለቲካ ቁርጠኝነት የሚጠይቀውን፣ በዓለም ላይ 119 ሀገራት ያላቸውን (አፍሪካ ውስጥ ከ55ቱ 35ቱ ሀገራት አላቸው)፤ እና የትምህርት ቤቶች ደኅንነት መጠበቅ ያለበት መሆኑን የሚደነግግ አዋጅ (Safe Schools Declaration) የሌላቸው ሀገራት መኖራቸውንና ያላቸውም ቢሆኑ ወደ ተግባር መለወጥ አለመቻላቸውን በማንሳት ይወቀሳል።

ሌላውና በዚሁ በአፍሪካ የትምህርት ይዞታና ሁኔታ ላይ የተደረገ ለየት ያለ ጥናት እንደሚያሳየው የአፍሪካ ትምህርት ችግር ዘርፈ ብዙ ነው። ይኸው የSilas Nkala ጥናት እንደሚለው ከሆነ፣ በአፍሪካ የሴቶች ተሳትፎ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ለዚህ ማሳያው ደግሞ በአፍሪካ ከ19 ሚሊዮን በላይ ልጃገረዶች ከትምህርት ገበታ ውጪ መሆናቸው ነው። የዚህ ትልቁ ምክንያት በቂ በጀት አለመመደብ ሲሆን፣ ይህም አሕጉሪቱ ለትምህርት ልታውለው ከምትችለው በጀት ላይ 29 ቢሊዮን ዶላርን በታክስ ማጭበርበር (tax abuse) ምክንያት እንድታጣ መደረጉ ነው።

በአፍሪካ ሥርዓተ-ፆታን ማመጣጠን ላይ ያለው ክፍተት አስደንጋጭ ነው። በአፍሪካ 38 ሚሊዮን 904 ሺህ 483 ልጆች ከትምህርት ቤት ውጪ ሲሆኑ፤ ከእነዚህ ውስጥ 18 ሚሊዮን 846 ሺህ 517 ያህሉ ልጃገረዶች ናቸው። እንደ ሌሎች በተለይ፣ የአፍሪካን ትምህርት ቅድመ- እና ድህረ- ቅኝ አገዛዝ በማለት ያጠኑቱ ጥናቶች ግኝት ከሰሐራ በታች ባሉት ሀገራት ሴቶች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን እንኳን ቢያጠናቅቁ (ተደራሽ ቢሆንላቸው) በቀጣናው ያለው የእናቶች ሞት 70 በመቶ ይቀንስ ነበር።

በብዙዎች ዘንድ እንደሚታመነው 55 አባል አገራትና ከ1 ነጥብ 4 ቢሊዮን በላይ ሕዝብ ባላት አፍሪካ ያለው የትምህርት ተደራሽነት በራሱ ችግር ያለበት ነው። ተደራሽ ሆኗል የተባለው ትምህርት እራሱ በጥራት ችግር የተተበተበ ሲሆን፣ በዚህ በኩል በከፍተኛ ደረጃ መሥራት የአሕጉሪቱ ኃላፊዎች ኃላፊነት ይሆናል።

ሌላው ችግር ለትምህርት የሚጠየቀው ክፍያ ነው። በአሕጉሪቱ ያሉና ለትምህርት የደረሱ ልጆችን ከትምህርት ገበታቸው ውጪ የሚያደርገው ከባድ ችግር ከጣራ በላይ የሆነው ክፍያ ሲሆን፤ በአሁኑ ሰዓት በዚህ ችግር ምክንያት ብቻ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ልጆች እየተማሩ አይደለም።

ይህ በቀጥታ በትላልቅ ኩባንያዎች አማካኝነት በታክስ ማጭበርበር የሚጠፋውና ከላይ የተጠቀሰው የ29 ቢሊዮን ዶላር ኪሳራ ውጤት ነው።

አፍሪካ በየዓመቱ ይህንን ያህል ገንዘብ ባታጣ ኖሮ በክፍያ ማጣት ምክንያት ሚሊዮኖች ከትምህርት ቤት ውጪ ሆነው እቤታቸው አይውሉም ነበር። አፍሪካ በአጀንዳ 2023 እና ስትራቴጂክ እቅድ (CESA 2016–2025) ውስጥ "አሳካዋለሁ ብላ የያዘችው እቅድም በተሳካ ሁኔታ በሄደም ነበር።

ከላይ በጠቀስናቸው ጥናቶች ግኝት መሠረት በአሕጉሪቱ ትምህርትን ለማዳረስና በተገቢው መንገድ ለማስኬድ ተጨማሪ 20 ከመቶ 29 ቢሊዮን ዶላር መመደብን ግድ ይላል። ይህ ደግሞ 25 ሚሊዮን ሕፃናት ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ መሠረታዊ ትምህርት የማግኘት ሰብዓዊ መብታቸውን እንዲያረጋግጡ ያስችላቸዋል።

ወደ መፍትሔው እየመጣ ያለው ይህ ባለ ብዙ ማጣቀሻዎች ጥናት እንደሚለው ከሆነ ሁሉም ነገር ከአሕጉሪቱ መሪዎች አናት ላይ የሚወርድ አይደለም። "መሪዎቻችን ይላል ጥናቱ "መሪዎቻችን ትምህርትን በተመለከተ ያላቸው አተያይ ግራ የሚያጋባ ነው። በቂ የሕግ ማዕቀፍ የላቸውም፤ በአህጉሪቱ በፖሊሲ የተደገፈ አሠራር ማየት ብርቅ ነው፤ በቂ በጀት አይመድቡም፤ ለሙስና የተጋለጡ አሠራሮችን አይቆጣጠሩም ወይም ለሙስና በራቸው በጣም ክፍት ነው።

በዚህ ጥናት ላይ በዋቢነት የተጠቀሱት የትምህርት ዓለም አቀፍ አፍሪካ (EIA) ዳይሬክተር ዴኒስ ሲንየሎ እንደሚሉት በአፍሪካ የመምህራን ልማት ላይ ከፍተኛ ችግር አለ፡፡ እጥረቱ ሰማይ ነው። የአፍሪካ መሪዎች በአስቸኳይ እነዚህን ችግሮች በመፍታት የአሕጉሪቱን የትምህርት ሕመም መታደግ አለባቸው።

እንደ ዳይሬክተር ዴኒስ አስተያየት የአፍሪካ መሪዎች በድርጅታቸው (AU) አማካኝነት እያንዳንዱ የአፍሪካ ልጅ ተገቢ የሆነ ትምህርት በተገቢና የሠለጠኑ መምህራን አማካኝነት እያገኘ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥና ካላገኘ እንዲያገኝ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን መፈተሽ አለባቸው። ሲፈትሹም የመምህራኑን የሥልጠና ደረጃ፣ ባለሙያነት፣ ምቹ የትምህርት አካባቢ ስለ መኖሩ ሁሉ ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡

ጥናታዊ ሪፖርቱ በመውጫ አንቀፆቹ ላይ አንድ ለየት ያለ ጉዳይ ያነሳ ሲሆን፣ እሱም የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች፣ በተለይም ግብ 4 (MDGs 4)ን ለማሳካት በዓለም አቀፍ ደረጃ 44 ሚሊዮን የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን እንደሚያስፈልጉና ከዚህ ቁጥር ውስጥ አብዛኛው ለአፍሪካ መሆኑን ነው።

ይህ ብቻም አይደለም፣ የጥናት ሪፖርቱ በመዝጊያ አንቀፁ ላይ አፍሪካን ብቻ የተመለከተ ሀሳብ የሰነዘረ ሲሆን፣ እሱም "አፍሪካ ዓለም አቀፍ ግዴታ የሆነውን አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በ2030 እውን ማድረግ ካለባት አሕጉሪቱ ብቁ የሆኑ 17 ሚሊዮን መምህራን ያስፈልጓታል ያለው ነው። እነዚህ መምህራን ብቃት ብቻ አይደለም ሊኖራቸው የሚገባው ብቃትና ጥራታቸውን ተከትሎ ፅድት ያለ ደመወዝና ምቹ የሥራ አካባቢዎች ያስፈልጓቸዋል፡፡

ከተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይ አኳያ ብቻ በማየት በጉባኤው ላይ ስለ አፍሪካ ትምህርትና ሥርዓተ ትምህርት፤ እንዲሁም ትምህርትና የነገዋ አፍሪካ ምን ምን ጉዳዮች ተነስተው ነበር የሚለውን በጨረፍታ እናያለን።

በናይጀሪያ የሕፃናት ፓርላማ ምክትል አፈጉባኤ ኢብራሂም ዛና በተጠናቀቀው የኅብረቱ የመሪዎች ጉባኤ ላይ እንደ ተናገሩት በአገራቸው በከፋ ጦርነት ምክንያት ትምህርት ቤቶች ሲወድሙና ሕፃናት ላይ አደጋ ሲደርስ ተስተውሏል፡፡ የአሕጉሪቱ መሪዎች ለዚህ ለዘንድሮው ‹‹2024 year of education›› የሚል ስያሜ ለተሰጠው ውሳኔ ሙሉ ለሙሉ ተገዥ በመሆን ውሳኔውን ያለ ምንም መሸራረፍ ወደ መሬት ሊያወርዱ ይገባል።

ይህ ድርጊት በዚህ ከቀጠለ በአሕጉሪቱ የሚከተለው የትምህርት ተቋማት መውደም፣ መዘረፍ፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ሕፃናት፣ መምህራን፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ ሌሎች በትምህርት ዙሪያ የሚሠሩ ሁሉ ሳይቀሩ መገደል፤ በመጨረሻም የትምህርት ቤቶች ሙሉ ለሙሉ መዘጋት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የሚቀረው ነገር የአፍሪካን መጪውን የጭለማ ዘመን መጠበቅ ነው።

ሌላው አስተያየት ሰጪ በ"ሴቭ ዘ ችልድረን የፓን አፍሪካ ጽሕፈት ቤት ጊዜያዊ ዳይሬክተር እና የአፍሪካ ኅብረት ተወካይ መሐሙድ መሐመድ ሀሰን በአፍሪካ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ እንደሚገደሉ፣ የሽብር ወንጀል እንደሚፈፀምባቸው፣ ትምህርት ቤቶች በቦምብ እሩምታ እንደሚወድሙ የገለፁ ሲሆን፣ ሀሳባቸው በጉባኤተኞች ድጋፍን አግኝቶ አስቆዝሟል።

በአሕጉር አቀፍ የትምህርት ስትራቴጂ ለአፍሪካ (Continental Education Strategy for Africa (CESA)) አማካኝነት ወደ ተግባር ይቀየሩ ዘንድ የተዘረዘሩ አስራ ሁለት ነጥቦች ይፋ የተደረጉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በአሕጉሪቱ በየደረጃው የትምህርትን ተደራሽነትና ጥራትን ማረጋገጥ፣ የትምህርት መሠረተ ልማትን ማስፋፋት፣ የተማሪና መምህራንን ጤና መጠበቅ፣ የመልሶ ግንባታ ሥራዎችን መሥራት፣ ቴክኖሎጂን ማስፋፋትና መጠቀም፤ የመምህራንን ሥልጠና ማካሄድ፣ ጥራት ያለው የትምህርት አመራርን መስጠት ፣ጥራትን መሠረት ያደረገ የሥልጠና ሥርዓት መዘርጋት ይገኙበታል፡፡

የትምህርት ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ መሐይምነትን ከአሕጉሪቱ ለማጥፋት አሕጉር አቀፍ ዘመቻ ማድረግ፣ ሳይንሳዊና እውነተኛ መረጃዎችን ለመላው አፍሪካ ኅብረተሰብ በማሰራጨት ተደራሽ ማድረግ፣ የሂሳብና ሳይንስ ትምህርቶችን በተጠናከረ ሁኔታ ማስተማር፣ ሙያና ቴክኒክ (TVET) ተቋማትን ማስፋፋትና በተለያዩ ሙያዎች የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ማስፋፋትና የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በስፋትና በጥራት ማከናወን የሚሉትም ከአስራ ሁለቱ ነጥቦች ውስጥ ይካተታሉ፡፡

ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማጎልበት፣ በሁሉም የትምህርት እርከኖች የሰላም ትምህርትን ማስፋፋት፣ ግጭት አፈታትን ማስረፅ፣ የትምህርት ባለ ድርሻ አካላትን በሙሉ ማሳተፍ የሚሉትም በአስራ ሁለቱ ነጥቦች ውስጥ ተካተዋል፡፡

የአፍሪካ ትምህርትን ወቅታዊ ሁኔታና አጠቃላይ ይዞታ በተመለከተ በአንዲት የጋዜጣ ገጽ ላይ ሁሉንም ማስተናገድ አይቻልም። የሚቻለው የዘንድሮውንና ሰሞኑን የተካሄደውን፤ መላው አፍሪካውያንን የሚወክለውን የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ ቅድሚያነትን ይዞ የነበረው የአሕጉሪቱ የትምህርት ጉዳይ እንደ መሆኑ መጠን እሱን አስመልክቶ ለትኩረት ያህል ጥቂት ማለት ብቻ ነው። በመሆኑም፣ መሪዎቹ በ2050 ከ2 አፍሪካውያን 1ዱ እድሜው ከ25 ዓመት በታች፤ እድሜያቸው ከ0-18 የሆኑ ልጆችና ወጣቶች 1 ቢሊዮን የሚደርስ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት የዩኒሴፍ "Transforming Education in Africa: An evidence-based overview and recommendations for long-term improvements" ጥናት አመላክቷል፡፡

ስለዚህ እ.ኤ.አ 1800ዎቹና ከዛ በፊት እንደነበረው ትምህርት መዝናኛ (luxury) አለመሆኑን ከልብ በመገንዘብ መሪዎቹ ባሉት፣ በወሰኑት መሠረት እንደሚከውኑና በቃላቸው እንደሚፀኑ ይታመናል፡፡

# ‹‹የካፒታል ገበያ በግልም ሆነ በመንግሥት በኩል ያሉትን የፋይናንስ ፍላጎቶችን የሚያሟላ ነው ››

-የኢትዮጵያ ሰነድ መዋለነዋዮች ገበያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ጥላሁን እስማኤል (ዶ/ር)

ምሕረት ሞገስ

የካፒታል ገበያ የተለያዩ ጉዳዮችን ያካተተ ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በዋናነት መገለጫው የኩባንያ ባለቤቶች ለግለሰቦች ድርሻ የሚሸጡበት አክሲዮን ላይ ያተኮረ መሆኑን ባለሙያዎች ያመለክታሉ፡፡ ከኩባንያ ድርሻ ሽያጭ ባሻገር የብድር ሰነዶች ግብይትን ማለትም የግምጃ ቤት ሰነድ (የቦንድ ሽያጭን)ም ያካትታል፡፡

የካፒታል ገበያ የዓለም ሀገራት ዜጎቻቸው የንግድ ልውውጣቸውን እና ኢንቨስትመንታቸውን ለማስፋፋት ሰፊ ሚና የተጫወተላቸው መሆኑ ይነገራል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ከሃምሳ ዓመት በፊት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ በነበረበት ዘመን ጅምሮች የነበሩ ቢሆኑም፤ ደርግ ይከተል በነበረው ርዕዮተ ዓለም ምክንያት ሙሉ ለሙሉ ተቋርጦ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በድጋሚ ማቆጥቆጥ የጀመረው ይኸው የካፒታል ገበያ፤ ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ ደረጃ ሕግ ተበጅቶለት ቁጥጥር እየተደረገበት ወደ ተግባር ሳይገባበት ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በመንግሥት ደረጃ ትኩረት እየተሠጠው በመምጣቱ፤ አዋጅ ወጥቶለታል፡፡ የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 መውጣትን ተከትሎ ከአንድ ዓመት ወዲህ በኢትዮጵያም እውን የሚሆንበትን መሥመር እያገኘ መጥቷል፡፡

ገበያው ተዓማኒነት እንዲኖረው እና ኢንቨስትመንቱ እንዲበረታታ በሚል ከአዋጅ በተጨማሪ ፈቃድ የሚሰጥ እና ግብይቱ እንዲሳለጥ የሚያግዝ ተቋምም ተቋቁሟል፡፡ በተቋሙ ሥራ ከሚተዳደሩት መካከል ደግሞ የኢትዮጵያ ሰነድ መዋለነዋዮች ገበያ አንዱ ነው። የእዚህ የኢትዮጵያ ሰነድ መዋለነዋዮች ገበያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ጥላሁን እስማኤል ካሣሁን (ዶ/ር) ከተቋሙ መቋቋም ምክንያት ጀምረን፤ የካፒታል ገበያ ምንነት፣ ጠቀሜታውን እና ሌሎችንም ጥያቄዎችን አክለን ያቀረብንላቸው ሲሆን፤ ምላሻቸውን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡፡ መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡-በቅድሚያ ስለኢትዮጵያ ሰነድ መዋለነዋዮች ገበያ ቢያብራሩልን?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** የኢትዮጵያ ሰነድ መዋለነዋዮች ገበያ በዚህ ዓመት እንደ አዲስ የታሰበ አይደለም። በፕሮጀክት ቢሮነት ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር የተቀረፀ ነበር፡፡ የካፒታል ገበያ አዋጅ አንቀፅ 31 ላይ የኢትዮጵያ መዋለነዋዮች ገበያ በመንግሥት እና በግል በጋራ ይቋቋማል ይላል፡፡ አዋጁን ተከትለን ተቋቁመናል፡፡ እኛ የመንግሥትን ሚና ይዘን የግል ኢንቨስትመንትን እንስባለን፡፡

በመንግሥት በኩል ያለው የእኛ ኢንቨስተር የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ነው፡፡ ይህ የተቋቋመው ባለፈው ዓመት ሲሆን፤ አብዛኞቹ የመንግሥት እሴት እና እሴቶችን ይቆጣጠራል። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ (ኢ አይ ኤች)፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድን፣ ኢትዮ ቴሌኮምን እና ሲቢኢን እንደባለቤት ያስተዳድራል፡፡ ስለዚህ እኛንም የሚያቋቁመን እርሱ ነው፡፡

የግል ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፍላጎት እስካለ ድረስ መንግሥት ከ25 በመቶ ያልበለጠ እጅ ይኖረዋል። ሌላው ደግሞ የግል ዘርፉ ኢንቨስተር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በኮሜርሺያል ኮድ የምንተዳደር ኩባንያ ነን ማለት ይቻላል፡፡ ፍቃድ የመስጠትን እና ቁጥጥር የማካሔድን ሥራ የሚያከናውነው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ነው፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን እና እኛ እንለያያለን።

የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ተቆጣጣሪ ነው። እንደብሔራዊ ባንክ ማለት ነው፡፡ እኛ ደግሞ እንደንግድ ባንክ ነን ማለት ይቻላል፡፡ በመንግሥት ድጋፍ ብንቋቋምም የምንተዳደረው እንደግል ድርጅት ነው፡፡ በግልፅ የተቋቋምነው በኅዳር 2016 ዓ.ም አካባቢ ነው፡፡ አሁን የቦርድ ዳይሬክተር አለ፡፡ ሠራተኞችን እየቀጠርን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዋናው ሥራችሁ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** ካፒታል የሚፈልጉ ተቋማት ወደ ኢንቨስተሮች ወርደው ካፒታል ይሰበስባሉ፡፡ ኢንቨስተሮቹ ማለትም ሰነደ መዋለነዋዩን የሚገዙት፤ አንደኛው መዋለ ነዋይ አክሲዮን ነው፤ አክሲዮኖችን ይገዛሉ፡፡ ሌላ ሰነደ መዋለነዋይ ደግሞ ቦንድ ነው። ሌላኛው ደግሞ የግምጃ ቤት ሰነድ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ኢንቨስተር ከገዛ በኋላ ወዲያው ትርፍ (የሚያገኘው ፈሳሽ ገንዘብ) የለውም፡፡ ለምሳሌ ቀደም ሲል አንድ የግምጃ ቤት ገዢ ሰነድ እስከሚያተርፍ ልጠብቅ ካለ 360 ቀን፣ ወይም 90 ቀን መቆየት ግድ ይለዋል፡፡ ቦንድ ከሆነ እስከ ቦንዱ ማጠናቀቂያ፣ አክሲዮን ከሆነም ትርፉ በአክሲዮን የትርፍ ክፍፍል እስከሚደርሰው ይጠብቃል፡፡

ከድሮ ጀምሮ አሜሪካን ውስጥ ወይም ያደጉ ሌሎች አገሮች ላይ ሰዎች አክሲዮን ይሻሻጡ ነበር። ይሻሻጡ የነበረው ገበያ ዛፍ ጥላ ሥር፣ ካፍቴሪያ ወይም አንድ ሆቴል ውስጥ ሆነው ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥም በተመሳሳይ መልኩ በ1960ዎቹ አካባቢ ብሔራዊ ባንክ እየተቋቋመ በነበረበት ጊዜ፤ አክሲዮን ገበያ ፈጥረው ብሔራዊ ባንክ ውስጥ ሰዎች ይገበያዩ ነበር፡፡

አሁን ደግሞ እኛ ኤሌክትሮኒክ የመገበያያ መድረክ እየፈጠርን ነው፡፡ ከሌላ ሰው ላይ ብዙ ሺህ ሰዎች አክሲዮን መግዛት እና መሸጥ ይፈልጋሉ። የእኛ አሠራር ሰዎች ወደ ኤሌክትሮኒክ ገበያ መጥተው ሰነድ መዋለ ነዋዮችን እንዲሻሻጡ ያስችላል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዋናው ጉዳያችን ዝውውር (liquidity) መፍጠር ነው። አንዱ ሻጭ ሌላው ገዢ የሚሆንበትን ምቹ ሁኔታ ማዘጋጀት ነው ብለን መውሰድ እንችላለን።

ከዚህ በፊት ቦንድንም፣ የግምጃ ቤት ሰነድንም ሆነ አክሲዮንን መሐል ላይ ለመሸጥ የሚፈልግ ግብይት የማካሔጃ መንገድም ሆነ ቦታ አልነበረውም፡፡ አሁን ግን አንዳንዶች ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ በቴሌግራም እና በኋዋትስአፕ የሚሻሻጡበት አካሔድ አለ፡፡ ይህ ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ ሲሆን፣ አንደኛ ውድ ነው፤ ሁለተኛ አደጋ አለው፡፡ በአጠቃላይ ግን የሰነደ መዋለነዋይ ገበያ ተቋም ማለትም የእኛ ተቋም ሥራ ይህንን ገበያ ያደራጃል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉንም አክሲዮኖች እና ቦንዶችን ከወረቀትነት እና ከቁስ አካልነት ወደ ቁስ አልባ አካልነት እንቀይርና ኤሌክትሮኒክ መዝገብ ውስጥ እናስቀምጣቸዋለን፡፡ ከዛ ኢንቨስተሮች መግዛት እና መሸጥ ሲፈልጉ፤ እንደማንኛውም ገንዘብ እንደማስተላለፍ ይሆናል ማለት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ይሔ ለማን ምን ይጠቅማል?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** ዋናው ሰዎች ተደፋፍረው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ይረዳል፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ ኩባንያዎቹ ባለሥልጣኑ ጋር መጥተው የኢንቨስትመንት መግለጫቸውን ያስመዘግባሉ፡፡ ከዛ ሕዝብ ጋር ወርደው አክሲዮን ይሰበስባሉ፡፡ ሕዝቡ አክሲዮን ከገዛ በኋላ ደግሞ፤ መሸጥ እና መግዛት የሚፈልግ ወደ እኛ ይመጣል ማለት ነው፡፡ ሰዎች ወደ እኛ ገበያ የሚመጡት በአገናኝ አማካኝነት ነው። ነገር ግን በዚህ ዘመን በተንቀሳቃሽ ስልክ አፕልኬሽን እና ዌብሳይቶች አሉ፡፡ ስለዚህ ገበያው ላይ መጥተው በአገናኛ አባላቸው በኩል በተንቀሳቃሽ ስልካቸው መግዛት እና መሸጥ ይችላሉ፡፡

ስለዚህ ዋናው ሥራችን ለሁሉም ሰው በሚያመች መልኩ የአክሲዮን ገበያ ዝውውር (ስቶክ ኤክስቼንጅ)ን መፍጠር ላይ እናተኩራለን፡፡ የሰነድ መዋለነዋዮች ገበያ የአክሲዮን ገበያ ዝውውር ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ከማስቻል በተጨማሪ፤ ለዋናው ገበያ የተሳለጠ ግብይት ለመፍጠር ሰፊ አስተዋፅኦ አለው። ስለዚህ ኩባንያ ነን። ፍቃድ የሚሰጠን ባለሥልጣኑ ነው፡፡

የገበያ ጉዳይ ሲነሳ ለጊዜው ቢያንስ ሦስት ገበያዎች አሉን፡፡ አንደኛው የአክሲዮን ገበያ ነው፡፡ በእዚህ ውስጥ ከፍተኛ አቅም ያላቸውን የምንዘረዝርበት ዋና መድረክ ይኖራል፡፡ ከእዛም ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ኩባንያዎች የምናገበያይበት አነስተኛ ቦርድ ይኖራል። ሁለተኛው ደግሞ የዕዳ ሰነዶች ገበያ፤ የቦንድ ገበያ ይኖራል፡፡

ከመንግሥት አንፃር ስናየው የመንግሥት ቦንድ ለምሳሌ የመንግሥት የግምጃ ቤት ሰነድ የሚገዙት ባንኮች እና ኢንሹራንሶች ይኖራሉ፡፡ ባንኮች እና ኢንሹራንሶች ከገዙ በኋላ ከእነርሱ በቀላሉ ማንኛውም ሰው ከሞባይሉ ላይ እንዲገዛ እና እንዲሸጥ ዕድል እንሠጣለን፡፡ ስለዚህ ይህንን የዕዳ ሰነዶች ገበያ ላይ ዜጎች ተሳትፈው መግዛት ከቻሉ መንግሥትም ከውጪ ብድር እና ድጋፍ ላይ ከማዘንበል ይልቅ፤ በሀገር ውስጥ ፋይናንስ በጀቱን ለማሟላት ምቹ ሁኔታን ያገኛል ማለት ነው፡፡ የመንግሥት ንብረቶች ላይም ዜጎች በቀላሉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ዕድል ይፈጠራል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የካፒታል ገበያ ሥርዓት መርሑ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** ዋነኛው የካፒታል ገበያ ሥርዓት መርሑ በመንግሥት ደረጃ የፋይናንስ ምንጩ ምንድን ነው? ብሎ ማሰብ ነው፡፡ ለምሳሌ መንግሥት ግብር ይሰበስባል፤ ከዚያም አገልግሎት ይሠጣል። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን የምንተዳደረው ከግብር በሚገኘው ገቢ ብቻ አይደለም፡፡ በዘንድሮ ዓመት እንኳ ቢታይ በጀታችን ከ800 ቢሊዮን አልፏል። የታክስ ገቢያችን ግን ግማሹንም አይሸፍንም፡፡ ስለዚህ እርሱን ለማሟላት የውጪ ብድር እና ድጋፍ ከዛ ደግሞ አንዳንዴ የብሔራዊ ባንክ ብድር ላይ በመመሥረት በጀቱ እንዲሟላ እናደርጋለን፡፡

ከበጀት ጉድለት በተጨማሪ በሌላ በኩል ያልተሟላ የጊዜው ጥያቄ እና የሕዝብ ፍላጎት አለ፡፡ በቀላሉ ፍላጎትን ማሟላት አለመቻል፤ ወይም ክፍተት አለ፡፡ የካፒታል ገበያ ሥርዓት ጥቅሙ ያንን ክፍተት ለመሸፈን ያግዛል፡፡ ስለዚህ መንግሥት እስከ አሁን ቦንድ ሲሸጥ ወይም የግምጃ ቤት ሰነድ ሲሸጥ ብዙ ተሳታፊ አልነበረውም፡፡ አሁን የተሳታፊዎቹን ቁጥር ማስፋት ይቻላል፡፡

አንድ ተቀጣሪ የግምጃ ቤት ሰነድ ገዝቶ ላያውቅ ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ሺህ ወይም አምስት ሺህ ብር ባንክ ያስቀምጥ ይሆናል፡፡ ባንክ ተቀምጦ ሰባት በመቶ ወለድ ከመሰብሰብ ይልቅ፤  አሁን ለግምጃ ቤት ሰነድ መንግሥት አስር በመቶ ይከፍላል፡፡ በተጨማሪ ከግብር ነፃ ነው፡፡ ስለዚህ ባንክ ገንዘብ የሚያስቀምጥ ሰው የግምጃ ቤት ሰነድ መግዛት ይሻለዋል፡፡ ኩባንያዎች፣ ውጪ ያሉ ዜጎችም ሆኑ ኢንቨስተሮች አክሲዮን መግዛትም ሆነ በሽያጩ ላይ መሳተፍ ይችላሉ። በመንግሥት በኩልም አስፈላጊነቱን ስንመለከት የተጠራቀመ የረዥም ጊዜ የፋይናንስ ፍላጎትን ለማሟላት ዕድል ይሰጣል፡፡ ተቋሙ ኢንቨስተሮችን ያመጣል፤ መንግሥት ሰነዶችን ያቀርባል፡፡ ስለዚህ ያ ፍሰት ተሳትፎን ያበረታታል፡፡

በሌላ በኩል የግል ዘርፉም ከፍተኛ የፋይናንስ ክፍተት አለበት፡፡ ነጋዴዎች የሚሠሩት ግማሹን ከኪሳቸው፣ ግማሹን ከባንክ ብድር ወይም ከግለሰቦች ብድር ነው፡፡ ያም ሆኖ ከአስር ዓመት በላይ የሚመለስ የረዥም ጊዜ ብድር የሚያበድራቸው የለም፡፡ ባንኮች የሚያበድሩት ለአጭር ጊዜ ነው፡፡ ምክንያቱም ባንኮች ዋና ምንጫቸው ተቀማጭ ነው፡፡ አስቀማጩ ደግሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን አምጡ ሊላቸው ይችላል። ስለዚህ ለሃያ እና ለሠላሳ ዓመት ለድርጅት ገንዘብ አያበድሩም፡፡ ስለዚህ ይሔኛው የመዋለነዋዮች



ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

# ‹‹የካፒታል ገበያ በግልም ሆነ በመንግሥት...

**ከ9ኛው ገጽ የዞረ**

ገበያ ለዚህ መፍትሔ ይሰጣል፡፡

ኩባንያዎች አሁን የተሻለ ገንዘብ የማግኛ አማራጭ ይኖራቸዋል፡፡ የካፒታል ማርኬት ጥቅሙ ይሔ ነው። ባለሃብቶቹ አክሲዮን ሲገዙ በሚቀጥለው ዓመት አምጡ ብለው አይጠየቁም፤ ሻጮቹም ግዴታቸው የትርፍ ክፍፍል እንዲዳረስ ማድረግ ነው፡፡ በሌላ በኩል አክሲዮን ገዢዎች ደግሞ፤ እንደባለአክሲዮን ሆነን የድርጅቱ ዕድገት ላይ ሚናችንን እንድንወጣ ዕድል ይሰጣል፡፡ ስለዚህ በአጠቃላይ የግል ዘርፉ ያለበትን የፋይናንስ ክፍተት ያሟላል፡፡

አንዳንዴ ደግሞ የግል ድርጅቶች መሥራት ያለባቸው በጣም ለሀገር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ይኖራሉ፡፡ ስለዚህም የረዥም ጊዜ ብድር ሊፈልጉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የኃይል ማመንጫ፣ ማዳበሪያ ፋብሪካ፣ የወረቀት ፋብሪካ ላይ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍ እንፈልጋለን፡፡ ግን ደግሞ እነዚህ ላይ ለመሥማራት ከፍተኛ ፋይናንስ ያስፈልጋል፡፡ ትርፋቸውም በአንድ እና በሁለት ዓመት የሚታይ ላይሆን ይችላል፡፡ ከባንክ ተበድረው ሥራውን ለማከናወን ይከብዳቸዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ በኩልም ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡

አሁንም ቢሆን ብዙዎቹ ባንኮች የተቋቋሙት አክሲዮን ሸጠው ነው፡፡ በአጭር ጊዜ አትራፊ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ በረዥም ጊዜ ግን አትራፊ ናቸው። ስለዚህ ዋና ጥቅሙ በግልም ሆነ በመንግሥት በኩል ያለ የረዥም ጊዜ የፋይናንስ ፍላጎትን ማሟላት ነው። ግለሰብም ቢሆን ሁል ጊዜ ገንዘብ ያለው ሰው ሪል እስቴት ብቻ ገዝቶ አይችልም፡፡ በሌላ በኩል አነስተኛ ኢንቨስተሮች ሪል እስቴት መግዣ ገንዘብም ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ለልጆቻችንም ሆነ ለእኛ በረዥም ጊዜ ትርፍ የምናገኝበት ኢንቨስትመንት ስንፈልግ አቅም ካለን ሆቴል እንገነባለን። አቅም ከሌለን ደግሞ ሆቴል ከሚገነባ ሰው ጋር የአንድ ሺህ ብርም ሆነ የአምስት ሺህ ብር ድርሻ እንገዛለን። ይህን ማድረጋችን ለራሳችንም ሆነ ለኢንቨስተሮችም ጥቅም አለው፡፡ ስለዚህ ዋና ግቡ ይህ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ያለበት ደረጃ ምን ይመስላል? የሕግ ድጋፉና ያሉ ክፍተቶች ምን ይመስላሉ?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** አሁን ወዳለው አሠራር ከመምጣታችን በፊት በዋናነት ዛሬ ላይም ቢሆን ትንሽ ወደ ኋላ ብንቀርም ወደ 400 ሺህ አካባቢ ሰዎች የአክሲዮን ድርሻ እንዳላቸው ይገመታል። 30 ባንኮች እና 18 ኢንሹራንሶች የተቋቋሙት በአክሲዮን ማኅበር ተደራጅተው ነው፡፡ 400ሺውም ባለአክሲዮኖች የፋይናንስ ፈሰስ ይፈልጋሉ፡፡ እርሱን የማዘመን ሥራ እየሠራን ነው፡፡ ያንን ለማድረግ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ተቋቁሟል፡፡ ስለዚህ እነርሱ መመሪያ እያወጡ ነው፡፡ መመሪያው ለእኛ ፈቃድ የሚሰጡበት፣ ለአገናኝ አባላት ፍቃድ የሚሰጡበት፣ ለኢንቨስትመንት ባንኮች ፍቃድ የሚሰጡበት መንገድ ላይ ያተኮረ ነው። ስለዚህ የሕግ እና የፖሊሲ ዝግጅት አካባቢ ብዙም ክፍተት የለም፡፡

ዋናው ክፍተት፤ የኢንቨስተር የዕውቀት ደረጃ እንዲሁም አክሲዮን ሸጠው ኩባንያ የሚሆኑበት ሁኔታ ውስን መሆን ነው፡፡ ስለዚህ የተቋማትን አቅም ማጎልበት ይጠይቃል፡፡ ለምሳሌ በእኛ ድርጅት እንዲገበያይ የሚፈቀድለት ድርጅት ኦዲት የሆነ የፋይናንስ ሪፖርት ያስፈልገዋል። ምክንያቱም የምናገበያየው አክሲዮን የግድ ተዓማኒነት ያለው መሆን አለበት፡፡ የኮርፖሬት ማረጋገጫ መመዘኛዎችን ማሟላት ይጠበቅበታል። ያ ደግሞ ከዜሮ የሚነሳ አይደለም፡፡ አሁን ላይ ትንሽ እንቅስቃሴዎች አሉ። ግን ደግሞ ብዙ ክፍተቶች አሉ። ብዙ ርቀት መጓዝ ያስፈልጋል። አካውንቲንግን የሚያጠና እና የሚያዘምን ቦርድ ተቋቁሟል፡፡ ስለዚህ እነርሱ ብዙ የማሻሻያ እና የድጋፍ ሥራ እየሠሩ ነው። እኛ ቅድሚያ መደገፍ አለብን። ሌላውም መደገፍ አለበት፡፡ በኩባንያዎቹ በኩል ዝግጁነት ይጠይቃል፡፡

ሌላው ክፍተት ደግሞ ኢንቨስተር፤ የሚገዛውን ማወቅ አለበት፡፡ የግምጃ ቤት ሰነድም ሆነ ቦንድ እንዲሁም አክሲዮን ምንድን ነው? የእኔ መብቶች ምንድን ናቸው? ጥቅሙ ምንድን ነው? ከሌላ ኢንቨስትመንት ይሔ በምን የተሻለ ነው? በምን ይለያል? ለእኔም ለሀገሬም ምን ያህል ይጠቅማል? የሚለውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡



ስለዚህ በዚህ ላይ ትምህርታዊ ሥራ መሠራት አለበት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ ያለው ክፍተት እንዴት ይታያል?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** በእርግጥ በቴክኖሎጂ በኩልም ክፍተት ይኖራል፡፡ ነገር ግን ዋናው ጉዳይ ግለሰብ ጥቅም እስካገኘበት ድረስ ወደ ቴክኖሎጂውም ሆነ ወደ አክሲዮን ግዢ መምጣቱ አይቀርም፡፡ ለምሳሌ ሁኔታውን እየተከታተለ ባንክ ከማስቀመጥ፣ ሕንፃ ወይም መሬት ከመግዛት የተሻለ ነው ብሎ አወዳድሮ ይመጣል፡፡ ስለዚህ የእኛ ሥራ ዓላማው ግብ እንዲመታ ማስቻል ነው፡፡

የእኛ ሥራ ቴክኖሎጂን በተከተለ መልኩ አንድ ሰው የኢንቨስትመንት መጠኑ አነስተኛ ሆኖ በቀላሉ መግዛት እንዲችል እና እንዲሸጥ ማድረግ ነው፡፡ አንድ ሺህ ብርም፣ አምስት ሺህ ብርም ሆነ አስር ሺህ ብር ያለው ሰው ድርሻ መግዛት እንዲችል እናደርጋለን ስንል፤ በዋናነት ገበያውን የሚያገናኙ አካላት ይህንን ሥራ ይሠራሉ፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ‹‹አምስት ሺህ ብር አለኝ፤ ድርሻ መግዛት እፈልጋለሁ›› ሲል የት መግዛት እንደሚችል አገናኝ አካላት ያማክሩታል፡፡ እነዚህ አገናኞች ፍቃድ እየወሰዱ ነው፡፡ ፍቃዳቸውን ሲጨርሱ ደግሞ በቴክሎጂም ሆነ በሌላው መልክ ላይ ሥልጠና ይወስዳሉ፡፡

ስለዚህ ዞሮ ዞሮ በቀጣይ ከፍተኛ የመማር እና የማስተማር ሥራ መሠራት አለበት፡፡ እኛም የራሳችንን ሚና እንወጣለን፡፡ ነገር ግን ሰው ስለተማረ ብቻ ኢንቨስት አያደርግም፤ ማበረታቻ ይፈልጋል፡፡ ማበረታቻው ካለ ሰው ራሱን ለመማርም ለማስተማርም ዝግጁ ይሆናል። ይህ ማለት ግን እንደዚሁ ግር ተብሎ የሚደረግ ግብይት አለ ማለት አይደለም፡፡ ምክንያታዊ የሆነ ውሳኔ እንዲወስን ማስቻል አለብን፡፡

ሁለተኛ ከቴክኖሎጂ አንፃር ልምምዱ አለ፡፡ ለምሳሌ ምን ያህል ሰው የሞባይል ዋሌት ተጠቃሚ ነው? ቢባል በጣም ብዙ ሰው እየተጠቀመ ነው፡፡ የእኛ ገበያ ሥራው የሚሆነው ያንን ማስቻል ነው። ሰው በእጅ ስልኩ አክሲዮኖችን በቀላሉ ማየት እና ለምን እንደሚገዛቸው እስከገባው ድረስ የመግዛት እና የመሸጥ ውሳኔን ለመወሰን ቀላል እናደርግለታለን። ይህ ሲታይ እንደውም ሌሎች አገሮች ላይ ድሮ ከነበረው አካሄድ የእኛ የተሻለ ዕድል አለው፡፡ ብዙ ሰው ዘመናዊ የእጅ ስልክ (የስማርት ፎን) ተጠቃሚ ነው፡፡ በስልክ በኩል ብዙ መረጃ ያገኛል። ስልክ ለመጠቀም ርካሽ ነው፡፡ ቢያንስ ኢንተርኔት ለማየት ለማገበብ እና መረጃ ማግኘት እንዲችል እንሠራለን፡፡

በተጨማሪ በቀጣይ የዲጂታል አካዳሚ ይኖረናል። ሰዎች እያዩ በነፃ መጥተው ኮርሶችን የሚወስዱበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ከፋይናንስ ጀምሮ፤ የግል ፋይናንሳቸውን በተመለከተ እንዲሁም ቁጠባ ምንድን ነው? ለምን እቆጥባለሁ? ምን ያህል እቆጥባለሁ? ከቆጠብኩ በኋላስ ገንዘቤን ምን ላድርገው? የተሻሉ አማራጮች ምን አሉ? የካፒታል ገበያን የአክሲዮንንም ሆነ የቦንድን ገበያ ምንነት በተመለከተ የማስተማር ሥራን እንሠራለን። ያው ነገር ግን እንደተባለው ክፍተቱ አለ፡፡ ነገር ግን መሠረታዊው ጉዳይ የማበረታቻ ሥርዓቱን መፍጠር ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እስከ አሁን ከተቋቋማችሁ በኋላ ምን ሠራችሁ?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** ከተቋቋምን ገና ሦስት ወር አካባቢያችን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በዚህ ዓመት ማጠናቀቂያ ላይ ወይም በቀጣይ ዓመት መጀመሪያ መስከረም ሲጠባ ገበያውን በይፋ እናስጀምራለን፡፡ ስለዚህ ለእርሱ ከመንግሥት ካፒታል አግኝተናል፡፡ የግል ዘርፉን ካፒታል እያሰባሰብን ነው፡፡ ይሔንን በወር እና በሁለት ወር ውስጥ እናጠናቅቃለን። ማስታወቂያ እያወጣን ሰው እየቀጠርን ነው፡፡ በቢሮ በኩልም የቀድሞ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ቢሯችንም ይሆናል፡፡ ስቱዲዮ ያለበት ወለል የገበያ ቦታ ይሆናል፡፡

አሁን ሲስተም እየገዛን ነው፡፡ ዋና የገበያ ማካሔጃ ሲስተም በሚቀጥለው ሁለት እና ሦስት ወር ውስጥ መዘርጋት እንጀምራለን፡፡ አገናኝ አባሎቻችንን ማሠልጠን እንጀምራለን፡፡ ኢንቨስተር የማስተማር ሥራ በንቃት እንሠራለን፡፡ ይሔ ሁሉ አዲስ የተጀመረ ወይም በሁለት ወር ውስጥ የተሠራ ሥራ ቢመስልም፤ ነገር ግን ቀደም ያሉ የተጀመሩ ሥራዎች ነበሩ፡፡ የሥራ ዕቅድ እና የፋይናንስ ናሙናዎችን እንዲሁም ሕጎችን የማዘጋጀት ሥራዎችን ቀድመን ስላጠናቀቅን ግፋ ቢል በስምንት ወር አብዛኛውን ሥራ እናጠናቅቃለን። ዞሮ ዞሮ ክረምቱን ካሳለፍን በኋላ የግብይት ሥራው መጀመሩ አይቀርም፡፡

**አዲስ ዘመን፡-ቀድማችሁ ያሰባችሁት እና ችግር ሲሆንብን ይችላል ብላችሁ የገመታችሁት ምንድን ነው ?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** ከላይ እንደገለፅኩት የካፒታል ገበያ ምንድን ነው? እንዴት ለእኔ ይጠቅመኛል? ብሎ መረዳት እና ቶሎ ከእኛ ጋር በፍጥነት በመሔድ በኩል በግል ዘርፎች ላይ ትንሽ ክፍተት አለ፡፡ አንደኛው እርሱ ነው፡፡ ሁለተኛው የሠለጠነ የሰው ኃይል ችግር ነው። ትንሽም ብንሆን ሥራው ሲካሔድ 60 እና 70 ሰዎች ሆነን እንጀምራለን፡፡ ነገር ግን በዘርፉ ላይ የሠራ የሠለጠነ የሰው ኃይል የለም፡፡ ስለዚህ ሰዎችን አምጥቶ ማሠልጠን እና ማስተማር ይጠይቃል፡፡ ይህ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለባለሥልጣኑም ወደ ፊት ደግሞ አገበያይ ለሆኑት ባንኮች ሊያጋጥማቸው የሚችል ችግር ነው፡፡

እነርሱም ያንን ለማድረግ ብዙ ሥልጠና እየወሰዱ ነው፡፡ ለምሳሌ የእኛ ቡድን በንግድ ምክር ቤት በኩል ሲ አይ ኤስ የሚባል ሥልጠና ይወስዳል፡፡ በካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በኩልም ሥልጠና እየተሰጠ ነው። ያም ሆኖ ሰው በራሱ ዝግጁ ልሁን ብሎ ማሰብ አለበት። መገናኛ ብዙኃንም ከባለሥልጣኑ ጋር ሆነን የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ሥልጠና እንስጥ ብለን እየሞከርን ነው። የኢኮኖሚ ወይም የፋይናንስ ጋዜጠኝነት (ቢዝነስ ጆርናሊዝም) ላይ እንሠራለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ በሀገር ደረጃ የሚያመጣው ለውጥ ምን ያህል ይሆናል?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** መመዘኛችን ለአንዳንድ ሰዎች ወይም ኩባንያዎች የሚሆነው መጀመሪያ ከኪሳቸው ወይም ከባንክ ተበድረው ማግኘት ያልቻሉትን፤ ሀገር አቀፍ የሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሳተፉ ዕድል ከሰጠ ጥሩ ነው፡፡ ስለዚህ ሃሳብ ይዞ በትክክል ቢተገበር ለሕዝብ አዋጭ የሆነ ምርት በመንግሥትም ሆነ በግል ዘርፍ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ መንግሥት ቦንድ ሸጦ መንገድ ሊሠራ ይችላል፡፡ አዋጭ እስከ ሆነ ድረስ ለሁሉም ጥሩ ይሆናል። የግል ዘርፉም በራሱ አቅም ማድረግ ከሚችለው በላይ ሃሳብ አፍልቆ አክሲዮን ሸጦ ፕሮግራም ቀርፆ ድህነትን መቅረፍ ከቻለ ዋነኛው መለኪያችን እርሱ ነው፡፡

የካፒታል ገበያ በጣም አነስተኛ የሆኑ ታዳጊ ሀገራት ላይ ብዙም ሚና የለውም እየተባለ ይተቻል። ነገር ግን አፍሪካ ላይም ቢሆን ጥሩ ጥቅም አለው፡፡ ለምሳሌ ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት ኬኒያ ነበር። ኬኒያ ላይ የናይሮቢ ገበያ ላይ ብዙ አክሲዮን ሸጦ ካፒታል ሰብስቦ እዛም የሚፈለገውን ፕሮግራም ተግብሮ ለእኛ የሚበቃ ገንዘብ ይዞ መጥቷል፡፡ አትርፎ ኢትዮጵያ ላይ ደግሞ ኢንቨስት እያደረገ ነው፡፡ 100 ሚሊዮን ብቻ ሳይሆን በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ላይ ተሳትፎ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ካፒታል ገበያ ታዳጊ አገር ላይ እንኳ እንደዚህ ዓይነት ኢንቨስትመንቶች እንዲሳኩ ማድረግ ይችላል፡፡

በዓለም ላይ ደግሞ ሰፋ ያለ ነው፡፡ እያንዳንዱ ምርት ከአክሲዮን ጋር ተገናኝቷል፡፡ ለምሳሌ የምንገለገልባቸውን እያንዳንዱን ቁሳቁስ ስናይ ከአክሲዮን ገበያ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ለምሳሌ ጋዜጠኛ የሚቀዳበት የድምፅ መቅጃ ሶኒ ቢሆን በካፒታል ገበያ ያደገ የሶኒ ኩባኒያ ነው። የምንጠቀመው ስልክ አይፎን ቢሆን የአፕል ኩባንያ ነው። እያንዳንዳቸው በካፒታል ገበያ ያደጉ ናቸው፡፡ ትንንሽ ጋራዥ ውስጥ የቤተሰባቸው ቤት ውስጥ እየሠሩ የነበሩ ሰዎች፤ ሃሳቦቻቸውን ለሰዎች ሸጠው ካፒታል ሰብስበው ሰው ቀጥረው ሃሳባቸውን መተግበር ችለዋል። ከሀገራቸው አልፈው እኛን እያገለገሉ ነው፡፡ እነርሱ እንደዛ ካደረጉ፤ እኛ ለራሳችን እንዴት እናንሳለን? ዋናው ጉዳይ ይሄ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለግለሰብም ሆነ ለአገር አልፎ ተርፎ ለዓለም የሚጠቅም ነገር ሲያስገኝ የሚችል ለፈጠራ እና ለዕድገት የሚያመች፤ የካፒታል ገበያ ኢትዮጵያ ላይ ለመተግበር አልዘገየም?**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** ፖለቲካው ተቀያይሯል፡፡ ለምሳሌ በንጉሡ ጊዜ ወደ 17 አካባቢ ኩባንያዎች ነበሩን፡፡ ወንጂ ስኳር፣ አንበሳ ከተማ አውቶቡስ፣ ሳባ ጠጅ፣ አቢሲኒያ ባንክ እና ሌሎችም አክሲዮን ሸጠው ተደራጅተው ነበር። ይህ በ1904 ዓ.ም አካባቢ ነው፡፡ ነገር ግን ደርግ ሲመጣ የአክሲዮን ካምፓኒዎች ተወረሱ፡፡ ስለዚህ ድራሻቸው ጠፋ፡፡ ከዛ ለውጥ በኋላ በአክሲዮን ገበያ ደረጃ መረጃም ባይደራጅ አክሲዮን እየሸጡ ማደራጀት ተጀምሮ ነበር፡፡ ለምሳሌ አዋሽ ባንክ በ1994 ዓ.ም አካባቢ ተደራጅቷል፡፡ ስለዚህ ቀደም ማለት ይቻል ነበር፡፡ ለምሳሌ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት በ1990 አካባቢ ጀምረው ነበር፡፡ ቢያንስ የሥርዓት ለውጡን ተከትሎ ማስተግበር ይቻል ነበር። አሁንም ያው ቢዘገይም ከመተው መተግበር ይሻላል፡፡ ብለን ጀምረነዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ፡፡**

**ዶ/ር ጥላሁን፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ፋሽን

## ‹‹ሽፎን›› በኢትዮጵያውያን ሴቶች ስምን ተመራጭ ሆነ?

**ሰሚራ በርሀ**



‹‹ሽፎን›› የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ከኢትዮጵያውያን ሴቶች የአለባበስ ልማድና ባሕል ጋር ተስማምቶ ቀርቧል። ጥሬ እቃው ከውጪ ይገባል። በትክሻ ልክ ተሠርቶ፣ ከወገብ ጥንቅቅ ተደርጎ በልብስ ስፌት ባለሙያዎች ይስተካከላል፣ ከጉልበት እስከ እግር ጣት ዝርፍፍ ብሎ ቁርጭምጭሚትን ጭምር የሚሸፍን ነው። በላዩ ላይ ደግሞ አጠር ያለ ነጭ ነጠላ ሲደረብበት ልዩ ውበትን ያላብሳል። እድሜም ገደብ ሳይኖረው የሚለበሰው ሽፎን ሴቶች በእምነት ቦታ፣ የሠርግ ዝግጅት ላይ፣ ለአዘቦት ቀንም ጭምር ተመራጭ ያደርጉታል። ሽፎን ከቅርብ ግዜ ወዲህ ደግሞ በስፋት የባሕል አልባሳት ገበያው ውስጥ በስፋት ይታያል።

አብዱልከሪም አብዱልሰመድ ይባላል፤ ዜድ ኬ የሽፎን ዲዛይን ሱቅ ባለቤት ነው። ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን በጨርቆስ የገበያ ማዕከል የሀገር ባሕል ልብስ፣ በዘመናዊ መልክ የሚሠራ ‹‹ሽፎን›› እና ሌሎች ቀሚሶችን በመሥራት ለገበያ ያቀርባል፡፡ በሥራው አንድ ዓመት ከመንፈቅ ያለፈ ጊዜን አስቆጥሯል፡፡ ወቅቱ ከሽፎን ጨርቅ የሚሠሩ ልብሶች ተቀባይነት እያገኙ የመጡበት ጊዜ በመሆኑ ሙያውን ለወራት ከተማረ በኋላ ወደ ገበያው ተቀላቅሏል፡፡

ባለሙያው እንደሚናገረው ሽፎን ልብስ የሚሠራበት ጥሬ እቃ የሚመጣው ከዱባይና ከሕንድ ነው። ብዙ ሴቶች ከእነዚህ የሻማ ይዘት ካላቸው ጨርቅ የሚሠሩ አልባሳትን ምርጫቸው ያደርጋሉ። ብትን ጨርቁን (ጥሬ እቃ) ከእነዚህ ሀገራት በማስመጣት የሚሸጡ እና በስፌት ሥራ ለተሠማሩ ባለሙያዎች የሚያቀርቡ ነጋዴዎች ያሉ ሲሆን አብዱልከሪም ብትን ጨርቁን ከሚያስመጡ ነጋዴዎች ተቀብሎ ይሠራል ፡፡

እንደ አብዱልከሪም ገለፃ፤ ሽፎን የሚሠራበት ጥሬ እቃ የማኅበረሰቡን አለባበስ እንዲመች ተደርጎ በመሠራቱ ብዙዎች እንዲመርጡት ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ ፋሽን በተዋወቀበት ወቅት በተለምዶ እናቶች ‹‹ሽንሽን›› እያሉ የሚጠሩት ቀሚስ አይነት ተደርጎ ይሠራል፡፡ አሁን አሁን ደግሞ ወጣት ሴቶች የተለያየ ዘመናዊ ዲዛይን በመምረጥ ይጠቀሙታል።

‹‹ሽፎን በጨርቆስ ገበያ በብዙ አማራጭ ይገኛል›› የሚለው አብዱል ከሪም፤ ይህንን አልባስ ደንበኞች በሚፈልጉት ዲዛይን የሚሠሩ ባለሙያዎችም በስፋት እንደሚገኙ ይገልፃል፡፡

ሽፎን የተለያየ ስያሜ ያለው መሆኑን በመግለፅም በብዛት ከኢትዮጵያ የሀገር ባሕል ልብስ ዲዛይን ጋር ተመሳስሎ እንደሚሠራ ያስረዳል፡፡ ሽፎን በባሕሪው ዘርፋፋና ረዥም መሆኑን፤ በዚህ መልክ ሲሠራም ይበልጥ ውበት እንደሚኖረውም ይናገራል፡፡ አንገቱ ላይ በአራት ማዕዘን እና በ ‹‹ቪ›› ቅርፅ ይሠራል። ወገብ ሽንሽን፣ አስመራ ክሽ ክሽ ወይንም በጉልበት አካባቢ የሚጨመር በዲዛይን ተመጥኖ የሚሠራ ጨርቅ፣ በዘመናዊ መንገድ ከሚሠሩ ደግሞ ሬድሜድ ቅድ በአሁን ሰዓት ደግሞ በአዘቦት ቀን መለበስ እንዲችሉ ቀለል ያለ ዲዛይን እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

አብዱልከሪም ወደ ሱቁ መጥተው ትእዛዝ ከሚሰጡት ደንበኞቹ ባሻገር በተለያዩ ማኅበራዊ ድረ-ገጾች ላይ የሚይዘውን የጨርቅ አማራጭ ያስተዋውቃል፡፡ የሽፎን ጨርቁ ከመሠራቱ በፊት እና ተሠርቶ ቀሚስ ሲሆን የሚኖረው ውበት የተለያየ በመሆኑ አዳዲስ ዲዛይኖችን አስቀድሞ ሠርቶ የተለያዩ የፎቶ ሞዴሎች፣ አርቲስቶች እንዲያስተዋውቁት በማድረግ ደንበኞችን ለመሳብ እንዲሁም ለማስተዋወቅ ይጠቀምበታል። ደንበኞችም የተለያዩ ገጾችን በመመልከት የራሳቸውን ዲዛይን እና የጨርቅ አይነት ይዘው ወደ ሱቁ ጎራ ይላሉ፡፡

በአብዛኛው በበዓላት ወቅት፣ ጥምቀት፣ ሠርግ ሲሆን እንስቶች በቤተሰባቸው አንድ አይነት የሽፎን ቀሚስን ምርጫቸው ያደርጋሉ፡፡ በኅብረት ሲለበስም የተለየ ውበትን ይሰጣል፡፡ ከፍ ያለ ቁጥር ያለው ደንበኛ የሚያስተናግዱበት ወቅትም የጥምቀት በዓል ሲቃረብ መሆኑን አብዱልከሪም አንስቷል፡፡ ሽፎኑ ብትን ጨርቅ ሆኖ ወደ ሀገር የሚገባ ሲሆን በአብዛኛው ስድስት ሜትር፣ አልያም አራት ሜትር ተደርጎ ወደ ሀገር ይገባል፡፡ ለአንድ ሰው ከሦስት ሜትር እስከ ስድስት ሜትር የሽፎን ጨርቅ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ጨርቁ በባሕሪው የመሳሳት ባሕሪ ስላለው ሲለበስ ተጨማሪ ገበር ከውስጡ የሚደረግበት ሲሆን የገበሩ አይነትም የልብሱ ውበት ላይ የራሱ አስተዋፅዖ አለው፡፡ ከተመረጠው የጨርቅ ቀለም ጋር አብሮ የሚሄድ የውስጥ ገበር እንዲሁም ልብሱን ይበልጥ እንዲያምር የሚያደረገው አንጸባራቂ የውስጥ ገበር በባለሙያዎች እይታ እና ምርጫ ይጠቀማሉ፡፡ የጨርቆቹ አይነት ወጥ የሆነ ቀለም እና በአብዛኛው ደግሞ ይህ ነው ተብሎ ሊለይ በሚችል ቀለም ላይ የተለያዩ አበባዎች አንጸባራቂ ፈርጦች ያሏቸው ናቸው፡፡

የሽፎን ጨርቅ በአንድ ሱቅ ውስጥ በሜትር ተለክቶ ከእነመሥሪያው እና ተጨማሪ ነጭ ነጠላ አብሮት ይዘጋጃል።፡ በአብዱልከሪም ሱቅ ከሦስት ሺህ 500 ብር ጀምሮ ለገበያ ቀርቧል፡፡ ልብሱን ሠርቶ ለማጠናቀቅ አንድ ሳምንት ጊዜን ብቻ ቢወስድም ተጨማሪ የቀን ቀጠሮ ለደንበኞች የሚሰጠው አስቀድመው የተሰጡ ትዕዛዞችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የሽፎን ጨርቅ መለመድ በሀገር ውስጥ የጨርቃ ጨርቅ አልባሳት ኢንዱስትሪ ላይ ተሠማርተው ለሚገኙ ባለሙያዎች ተጨማሪ የገቢ ምንጭን እንደፈጠረም የልብስ ስፌት ባለሙያው ይናገራል፡፡ አብዱልከሪም በሱቁ ውስጥ ከሽፎን ውጪ የሐገር ባሕል ልብስን አጣምሮ ይይዛል፡፡

የዝግጅት ክፍላችን ለልብስ ስፌት ባለሙያው ‹‹የሽፎን ጨርቅ መለመድ ደንበኞች ፊታቸውን ወደ ሀገር ባሕል ልብስ እንዳያዞሩ አላደረገም›› በማለት ላቀረበለት ጥያቄ ‹‹በሁለቱ የልብስ አይነቶች መካከል ውድድር እንዲፈጠር እና የሀገር ባሕል ልብሶች በተሻለ መልኩ ተሠርተው እንዲቀርቡ ያደርጋል›› ሲል ያመጣውን ጥሩ እድል ገልፆልናል፡፡ ደንበኞች ከሀገር ባሕል ልብስ ይልቅ ሽፎንን የመረጡበት ምክንያት ምናልባት ያልተዘጋጁበት ቀጠሮዎች ቢኖርባቸው በፍጥነት ተሠርቶ ማለቅ የሚችል እና በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት የሚችሉት ስለሆነ ነው ይላል፡፡

በጨርቆስ አካባቢ ባሉ የገበያ ማዕከሎች አብዛኞዎቹ ሱቆች የሽፎን ጨርቆች የሚይዙ ሲሆን የልብሱ መለመድ እና በሀገር ውስጥ ባለው የአለባበስ አይነት የሚስተካከል እና የሚመች ተደርጎ መሠራቱ ‹‹የሀገር ባሕል ልብስ ገቢው እና በዘርፉ የተሠማሩ ባለሙያዎች ላይ ተፅዕኖ ያሳድር ይሆን›› የሚል ጥያቄ መፍጠሩ የማይቀር ነው፡፡

ወይዘሮ ዓለምፀሐይ መብራቴ የሀገር ባሕል አልባሳት በተለያየ መልኩ ዲዛይን በማድረግ በመሸጫ ሱቃቸው ለደንበኞች ያቀርባሉ። እርሳቸው እንደሚሉት ተጠቃሚዎች ሽፎንን የሚመርጡት በሀገር ባሕል አልባሳት ላይ ፍላጎት አጥተው ሳይሆን በሁለቱ መሐከል ያለው የዋጋ ልዩነት ሰፊ በመሆኑ ነው፡፡

‹‹ሰዎች አሁንም ቢሆን የሀገር ባሕል ልብስን ይመርጣሉ፡፡ ነገር ግን የዋጋው መወደድ ወደ ሽፎን እንዲዞሩ ያደርጋቸዋል›› የሚሉት ወይዘሮ ዓለምፀሐይ ምክንያቱን ይገልፃሉ። የሀገር ባሕል ልብስ ለመሥራት የሚያገለግሉ ግብዓቶች መወደድ ለዋጋው መናር ሚና ስላላቸው ደንበኞች በተመጣጣኝ ዋጋ የቀረበውን የሽፎን ጨርቅን እየመረጡ መሆኑንም ተናግረዋል።

ከቅርብ ግዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የአልባሳት ገበያ ውስጥ ሽፎን ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ ነው። ይህ ፋሽን ከመለመዱ አስቀድሞ በገበያዎች ላይ የሀገር ልብስን ከቻይና በማሽን ተሠርቶ በሚመጣ ልጥፍ ጥበብ (በአቡጀዴ) ማቅረብ በተመሳሳይ ተለምዶ ነበር። አሁን ደግሞ የኢትዮጵያን የሴቶች የባሕል ልብስ ሽፎን በቀዳሚነት እየመራው ይመስላል። ሰላም!!

# ትዝብት/ ማረፊያ

## እንዴት በሁሉም ዘርፍ ጉራማይሌ ሆንን?

**ዋሰልኝ አየለ**

‹‹ብዝኃነት›› የሚለውን ቃል ፖለቲከኞች በተደጋጋሚ ስለሚጠቀሙት ምናልባትም አሰልቺ የፕሮፖጋንዳ ቃል ሊመስል ይችላል፡፡ በነገራችን ላይ በፖለቲከኞች ምክንያት ለዘመናት ሲያገለግሉ የነበሩ ቃላት ተደራቢ ትርጉም እንዲይዙ ተደርጓል። መደበኛ ትርጉማቸውን በመርሳት ከፖለቲካ ጋር ብቻ የማያያዝ ልማድ ይዳብራል፡፡ ለምሳሌ፤ በኢሕአዴግ ጊዜ ‹‹ልማት›› የሚለው ቃል አሰልቺ ሆኖ ነበር፡፡ ልማት የሚለውን ቃል ግን የኢትዮጵያ ገበሬ ለዘመናት ሲጠቀመው የኖረ ነው። በተለይም በመስኖ የሚለሙ ነገሮችን ‹‹ልማት›› እያለ ይጠራቸዋል። አርሶ አደሩ ልማት የሚለውን ቃል ያመጣው ልምላሜ ከሚለው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለምለም፣ ለምለሚቱ፣ ለማ... የሚሉ የሰው ስሞች ይወጣሉ፡፡ በአጭሩ ልማት የሚለው ቃል አረንጓዴን፣ ልምላሜን፣ ብዛትን፣ ጥሩ ነገርን የሚገልጽ ነው፡፡

ልማት የሚለውን ቃል ኢሕአዴግ በየመድረኩ ስለሚጠቀመው እየተሰለቸ መጣ፤ እንዲያውም በኋላ አካባቢ ልማት የሚለውን ቃል መጠቀም የካድሬነት መለያ እስከሚመስል ድረስ ቃሉ መቀለጃ ሆነ፡፡ አሁንም ‹‹ብልጽግና›› የሚለውን ቃል ከአሁኑ ገዥው ፓርቲ ጋር በማያያዝ የፓርቲው ብቻ እየተደረገ ነው። ብልጽግና የሚለው አማርኛ ግን ለዘመናት ሲያገለግል የቆየ ነው፡፡ ፖለቲካና ቃላትን በተመለከተ በሌላ ጽሑፍ እንመለስበታለን፡፡

የኢትዮጵያ ብዝኃነት ባሰቡት ቁጥር የሚያስገርም ነው፡፡ ኢትዮጵያ አንድ ሀገር ብቻ አይደለችም፤ ሁሉንም ሀገር ነች፡፡ የምዕራቡን ዓለም፣ የምሥራቁን ዓለም፣ የዓረቡን ዓለም... ሁሉ በየዓይነቱ የያዘች ናት። በመስከረም ወር ውስጥ እንዳስነበብነው፤ ኢትዮጵያ ማለት በአንድ ወር፣ በአንድ ቀን፣ በአንድ ሰዓት እና በአንድ ደቂቃ ውስጥ እንደ ራስ ዳሸን ተራራ አይነት የሚያንዘፈዝፍ ብርድ ያለባት፣ በዚያው ቅጽበት እንደ ዳሎል ያለ እንደ እሳት ላንቃ የሚገርፍ ሙቀት ያለባት ናት፡፡ በዚች ሰዓት በዚች ቅጽበት ሙቀት ያለባት፣ ብርድ ያለባት ናት፡፡ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ጣርማ በር አካባቢ ጉም እና ብርድ ያለበት፣ በዚሁ አካባቢ ሸዋ ሮቢት ሙቀት ያለባት ናት። በባሌ ተራሮች፣ በከፋ ዞን ጫካዎች ብርድ ያለባት፣ በድሬዳዋና ጅግጅጋ አካባቢዎች ሙቀት ያለባት ናት። በተመሳሳይ ቀን ደብረ ብርሃን ብርድ ነው፤ አዳማ ሙቀት ነው፡፡ ይህ በተፈጥሮ ያገኘነው ፀጋ ነው፡፡

የሰዎችን ባሕልና ልማድ ደግሞ ልብ እንበል። በእርግጥ ባሕል እና ልማድ ተፈጥሮን መሠረት ሊያደርግ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ግን አዋሳኝ አካባቢዎችንና ጎረቤት ሀገራትንም መሠረት ያደርጋል። በዚህም ምክንያት የሰሜን ኢትዮጵያ እና የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የምዕራብ ኢትዮጵያ እና የምሥራቅ ኢትዮጵያ የተለያየ ባሕልና ሥነ ልቦና ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

አካላዊ ገጽታዎቻችንም ከፍተኛ ብዝኃነት ያለባቸው ናቸው፡፡ በጥቅሉ ‹‹ጥቁሮች›› ተብለን ብንጠራም ልክ እንደ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ተመሳሳይ ፊትና ጥቁረት ያለን አይደለንም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ቀይ የቆዳ ቀለም ያለው አለ፣ ነጭ የቆዳ ቀለም ያለው አለ፣ ጥቁር የቆዳ ቀለም ያለው አለ፣ ጠይም የቆዳ ቀለም ያለው አለ፡፡ የፊት ቅርጽ የተለያየ አይነት አለ፡፡ በቁመትም ብዝኃነቱ የበዛ ነው፡፡

እነዚህ በተፈጥሮ የተገኙ ብዝኃነቶች ለሰው ሠራሽ ብዝኃነትም ምክንያት የሆኑ ይመስላል። ምንም እንኳን ሀብታም እና ድሃ በሁሉም ሀገራት ቢኖርም ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ልዩነቱ የበዛ ይመስላል፡፡ ከአንድ ትልቅ ሆቴል አጠገብ የሚበሉት አጥተው የሚለምኑ የሚገኙት ኢትዮጵያ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ብዙ በምቾት የሚኖር፣ ብዙ በስቃይ የሚኖር፤ ብዙ ከልክ በላይ የሚመገብ፣ ብዙ በረሃብ የጠወለገ ያለባት ናት፡፡

በተፈጥሮ የተገኙት ብዝኃነቶቻችን ፀጋዎች ናቸው፤ ኢትዮጵያን በዓለም እንድትታወቅ የሚያደርጉ የተፈጥሮ ስጦታዎች ናቸው፡፡ ተፈጥሮንና አካባቢን ተከትሎ የተገነቡት የባሕል ብዝኃነቶቻችንም ውበታችን እና ኩራቶቻችን ናቸው፡፡ በዚያው ልክ የአስተሳሰብና የሥነ ልቦና ልዩነት መፈጠሩም ውበት ነው፤ ተፈጥሯዊ ነው፡፡

አስቸጋሪ እና አደጋ የሆነው ግን የአስተሳሰብ ልዩነቶቻችን መረን የለቀቁ እየሆኑ ነው፡፡ ጫፍና ጫፍ የረገጡ ተፃራሪ አመለካከቶች እየበዙ ነው፡፡ የአመለካከትና አስተሳሰብ ልዩነት ተፈጥሯዊ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየገነገኑ የመጡት ግን ለሀገር አደጋ የሚሆኑ ናቸው፡፡ የጋራ ታሪክ ላይ፣ የጋራ ሀብት ላይ፣ የጋራ ሀገር ላይ የማይታረቁ የሚመስሉ መካረሮች እየታዩ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ በአንድ የጋራ ታሪክ ላይ በሀሳብ ልዩነት ከመወያየትና ከመከራከር ይልቅ አንደኛው ወገን የማምለክ ያህል ያደንቃል፣ አንደኛው ወገን ከታሪክ ገጽ መፋቅ አለበት ይላል፡፡ በዚህ መሐል የዚያ ታሪክ እውነታ ዋጋ ያጣል ማለት ነው፡፡ ሁለቱም የየራሳቸውን ፍላጎት ብቻ በመከተል ከእውነተኛ ክስተቱ ውጭ ያደርጉታል። ይህ ደግሞ ሌሎች የተበላሹ ትርክቶችን እየፈጠረ የሌላ ሀገር እና የሌላ አገር ዜጎች የሆንን ያህል ያራርቀናል ማለት ነው። ልዩነታችን የውበት ሳይሆን የጥፋት ይሆናል ማለት ነው፡፡

ከፍተኛ የሆነ የሞራል ልዕልና ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፤ በዚያው ልክ ግን ከፍተኛ የሆነ የሞራል ዝቅጠት እየታየ ያለውም ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ለአስከሬን ክብር ያለው ሀገር ያለ አይመስልም፤ በዚያው ልክ ግን አስከሬን በገመድ ሲጎተት እና አስከሬን ሲሰቀል ያየነውም እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነ፡፡ አልጋውን ለእንግዳ ለቆ መሬት ላይ የሚተኛ ሕዝብ ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፤ በዚያው ልክ ግን ከመሬቴ ውጣ የሚል ዘግናኝ ግድያ ያየነውም እዚሁ ነው፡፡

እነዚህኞቹ ልዩነቶቻችን ግን ከውበታዊ ልዩነቶቻችን የመጡ አይደሉም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው ልዩነት ውበት መሆኑን የማይረዱ ፖለቲከኞች በሚነዙት የጥላቻ ስብከት የተገነቡ ናቸው፡፡ ይህ የእገሌ እንጂ የአንተ አይደለም፤ ይህ የአንተ እንጂ የእገሌ አይደለም... የሚል አስተሳሰብ ባላቸው ዋልታ ረገጥ ፖለቲከኞች የተነዛ ትርክት ነው እንዲህ አይነት አጥፊ ልዩነቶችን የፈጠረው።

ይህ ባይሆን ኖሮ በሁሉም ዘርፍ ጉራማይሌ መሆናችን የልዩነት ሳይሆን የውበት ምንጭ ነው። የተፈጥሮና መልክዓ ምድር ልዩነታችን፣ የባሕልና ወግ ልዩነቶችን፣ የአካላዊ ገጽታ ልዩነቶቻችን ሁሉንም ያሟልን እንድንሆን ያደርገናል፡፡ ደጋውንም ቆላውንም ወይና ደጋውንም ማሟላት መታደል ነው። ጠይሙንም፣ ቀዩንም፣ ጥቁሩንም መያዝ መታደል ነው፡፡ እነዚህን መታደሎቻችንን ግን የአስተሳሰብ ልዩነቶችንም እንደ ውበት በማየት እንድገመው!

## ነፃ ሃሳብ

# የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች...

ከገጽ 5 የዞረ

ለማፍራት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ለውጭ ባለሀብቶች ቅድሚያ መሰጠቱ ትክክልም ተገቢም ነው፡፡

ይህ ሀሳብ የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ ኢትዮጵያ ከአጎዋ እስከ ታገደችበት ጊዜ ድረስም በርካታ ስመ ጥር የውጭ ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ገብተው ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እያቀረቡ ሀገሪቱም የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ አስችለዋል። ሌሎች በርካቶችም ሼዶችን በመያዝ ወደ ሥራ ለመሠማራት ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ መንግሥት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ በስፋት ገብተው የሚሠሩበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ይህን ተከትሎም ጥቂት የማይባሉ ባለሀብቶቹ ወደ ፓርኮቹ እየገቡ ናቸው፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽንን መረጃ ዋቢ ያደረገው ይህ ጋዜጣ ይዞት የወጣ ዘገባ እንዳመለከተው፤ ኮርፖሬሽኑ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ሥራዎች ላይ የሚሠማሩ ባለሃብቶችን ቁጥር ለመጨመርና ከኢንቨስተሮች ጋር ያለውን ትስስር ለማሻሻል አዳዲስ የሪፎርም ተግባራትን ጨምሮ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ እነዚህ ተግባራትም ብዙ ባለሃብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹና ወደ ድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና እንዲገቡ ማድረግ ችለዋል፡፡

ባለፈው አንድ ዓመት በልዩ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቷቸው ከተከናወኑ ተግባራት መካከል አንዱ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን የማነቃቃት፣ የማበረታታትና ወደ አምራች ዘርፉ ገብቶ ውጤታማ ሥራዎችን እንዲሠራ የማድረግ ሥራ ነው፡፡ በዚህ ሂደት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ወደ አምራች ዘርፉ እንዳይገቡ መሰናከል የነበሩ ችግሮችን በመለየት መፍትሔ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

በቅርቡ ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለመሥራት ከኮርፖሬሽኑ ጋር ስምምነት ካደረጉት አስራ አንድ ኩባንያዎች መካከል አብዛኞቹ ሀገር በቀል ኩባንያዎች ሲሆኑ፣ በ2016 ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከገቡ አምራቾች መካከል ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ናቸው፡፡

በ2015 እና 2016 ዓ.ም የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች እንዲነቃቁ፣ ባለሃብቶቹ ያሉባቸውን የፋይናንስና ሌሎች ክፍተቶችን የሚሞሉ ተግባራት ተከናውነዋል። በመሆኑም በ2015 እና ዘንድሮ ከተመዘገቡት ባለሃብቶች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ሁሉ መረጃዎች ሲታሰቡ የሀገር ውስጥ አምራቾች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እንዲገቡ የተሰጠው ትኩረት ውጤት እያሳየ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የግሉ ዘርፍ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጪ ባሉት የአምራች ኢንዱስትሪው ሼዶች እንዲሁም ራሱ በየክልሉ በሚገነባቸው ፋብሪካዎች የኢንዱስትሪው ዘርፍ ተሳታፊነቱ እየጨመረ ለመምጣቱ ከየክልሎቹና ከተሞቻቸው፣ ዞኖቻቸው የሚመጡ መረጃዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ሀገሪቱ ከውጭ የምታስመጣቸው በርካታ ምርቶች በሀገር ውስጥ እየተመረቱ ካሉበት ሁኔታም መረዳት የሚቻለው የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው እያሳየ ያለው ተሳትፎና እያከናወነ ያለው እየጨመረ መምጣቱን ነው፡፡

የኢትዮጵያን አምራች ዘርፍ እዚህ ደረጃ ለማድረስ ሀገሪቱ ብዙ ዋጋ ከፍላለች፡፡ በወታደራዊው አገዛዝ የኢትዮጵያ የግል ዘርፍ በአጠቃላይ ክፉኛ መመታቱ ይታወቃል፤ በኢሕአዴግ መንግሥት የማንሰራራት ሁኔታ ቢታይበትም፣ በመሬትና በመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ በመልካም አስተዳደር ችግሮች ሳቢያ በእጅጉ ተፈትኗል፡፡

በወቅቱ የነበረው መንግሥት የግሉ ዘርፍ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው እንዲሠማራ ጽኑ ፍላጎት ቢኖረውም፣ የግሉ ዘርፍ ከለተመደው የንግድና ሕንጻ ልማት ውጪ በኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ በኩል የሚታየው አልነበረውም፡፡ የቆየባቸው የምጣኔ ሀብቱ ዘርፎች ዘርፎች በቀላሉ የሚከበርባቸው መሆናቸው፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍ የዘርፉ እውቀት፣ ቴክኖሎጂና ልምድ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ በእጅጉ የሚፈልግ መሆኑ በወቅቱ ለነበረው የግል ዘርፍ በዚህ ዘርፍ መሰማራት አስፈሪ ነበር፡፡

ይህን አመለካከት ለመቀየርና ስጋቱን ለማስወገድም ሀገሪቱ ብዙ ሠርታለች፡፡ የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪው ቢሰማራ ራሱንም ሀገርንም እንደሚጠቅም በማመን፣ የግሉ ዘርፍም እንዲያምን በማድረግ ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ብዙ ሠርቷል፤ ለሀገርም ለባለሀብቱም በዘላቂነት የሚጠቅመው የአምራች ዘርፉ መሆኑን ብቻ አልነበረም ሲያስገነዝብ የነበረው፤ ማበረታቻዎችንም በማድረግ ባለሀብቱን ከንግድ ወደ አምራች ዘርፉ ለማሳብ ተሞክሯል፡፡

በመንግሥት እጅ ውስጥ የነበሩ በርካታ ኢንዱስትሪዎችን ለግሉ ዘርፍ በማዞር የግሉን ዘርፍ ለማበረታታት ተሠርቷል፡፡ መንግሥት የግሉ ዘርፍ አይደፍራቸውም ተብለው በሚታሰቡት እንደ ኤሌክትሪክ ኃይል ልማት ባሉት ላይ በማተኮር የግሉ ዘርፍ እንዲነቃቃ ለማድረግ ጥረት አድርጓል፡፡ ይህም ለግሉ ዘርፍ መነቃቃት የበኩሉን ሚና ተጫውቷል፡፡

በአምራች ኢንዱስትሪው የሚሠማሩ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች መጠን እየጨመረ መምጣት የቻለው ሀገሪቱ ለዘርፉ የሰጠችውን ይህን ሁሉ ትኩረት ተከትሎ በተከናወኑ በእነዚህ ሁሉ በርካታ ሥራዎች ነው፡፡ ይህ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የአምራች ዘርፉ ተሳትፎ እየተጠናከረ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

እነዚህ በአምራች ኢንዱስትሪው ተሠማርተው እየሠሩ ያሉ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ምርታማ በሚሆኑበት ላይ በትኩረት መሠራት ይኖርበታል፤ እነዚህ ባለሀብቶች በቀጣይ በአምራች ኢንዱስትሪው ለሚሰማሩ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች ፈር ቀዳጅ እንደመሆናቸው፣ ለእነሱ የሚደረገው ድጋፍ ከእነሱ የሚገኘው ውጤት ባለሀብቶቹ በዘርፉ እንዲቆዩ፣ ሌሎችን ባለሀብቶችንም እንዲከተሏቸው በማድረግ በኩል ትልቅ አቅም ይሆናል፡፡

ባለሀብቶቹ ብዙዎች የሚፈሩትን የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ደፍረው የገቡ እንደመሆናቸው እንደ ዓይን ብሌን መታየት ያለባቸውና ገና በዙ ድጋፍ ሊደረግላቸው የሚገባም ናቸው፡፡ ዘርፉ በውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ በኃይል አቅርቦት፣ በገበያ ችግር ተደናግጦ ከዘርፉ እንዳይወጣ ማድረግ ይገባል፡፡

ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ብዙ አስተዋፅዖ እያበረከተ ነው፡፡ ንቅናቄው ከጦርነትና ግጭት ከውጭ ጫና ጋር በተያያዘ ሥራ አቁመው የነበሩ በርካታ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንዲመለሱ ያስቻለ ነው፡፡ ይህ የንቅናቄው ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ተኪ ምርትን ዋና ጉዳይዋ አርጋ አተኩራ የምትሠራ ሀገር፣ ለውጭ ገበያ ማምረትን ሌላው ዋና ጉዳይዋ አርጋ የምትሠራ ሀገር ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ትኩረት መሰጠቷን አጠናክራ መቀጠል ይኖርባታል። ይህን በብዙ ዓመታት ድካም የመጣ የአምራች ዘርፉን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተሳትፎ የመጨመር ውጤት ይበልጥ እንዲጨምር ማድረግ ላይ መሠራት ይኖርበታል፡፡

በዚህ ተሳትፎ መጨመር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ የሚችል አንድም አይነት ተግዳሮት እንዳይኖር፣ ቢኖሮም ፈጥኖ ለማቃለል መሠራት ይኖርበታል፡፡ እስከ አሁን የተደረገውም ይሄው ነው። መንግሥት ዘርፉ በታሰበው ልክ አልሆነም ብሎ አልተወውም፤ ከዚህም ይልቅ የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ዘርፉን መደገፉን ነው የቀጠለው፡፡

አሁንም ይሄው ሥራ መጠናከር ይኖርበታል። የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለግሉ ዘርፍ ለማቅረብ የተከናወነው ተግባር አድናቆት ሊቸረው የሚገባ ሆኖ፣ በቀጣይ ሊኖር የሚችለውን የባለሀብቶች ፍሰት ታሳቢ ያደረገ ግንባታም ሆነ ዝግጅት አለመኖሩ ያሳስባል፡፡

የውጭ ባለሀብቶች ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ባላውቅም፣ የኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች የሼዶች ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱን መረጃዎች እያመለከቱ ናቸው፡፡ ይህ ፍላጎት ከእስከ አሁኑም በላይ ሊጨመር እንደሚችል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የታየው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የመግባት ሁኔታ ይህን ፍሰት ታሳቢ አርጎ መሥራት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል፡፡

በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባለሀብቶቹ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እየመጡ ያሉት ሀገር በተለያዩ ፈተናዎች ውስጥ በሆነችበት በአሁኑ ወቅት ነው። በግብዓት በውጭ ምንዛሪ እንዲሁም ከሠላምና ደህንነት ጋር ተያይዞ በርካታ ፈተናዎች በሀገሪቱ ባሉበት ወቅት ነው፡፡

ሀገር በእዚህ ፈተና ውስጥ አትቀጥልም፤ መንግሥት እያከናወነ ባላቸው ተግባሮች ተግዳሮቶቹ ሊወገዱ የሠላምና ፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ሠላም ደኅንነት ሊሰፍን ይችላል፡፡ ያኔ ደግሞ ወደ አምራች ኢንዱስትሪው በተለይም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚመጡት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በእጅጉ ሊጨምር ይችላል፡፡

ሀገር በእዚህ ፈተና ውስጥ አትቀጥልም፤ መንግሥት እያከናወነ ባላቸው ተግባሮች ተግዳሮቶቹ ሲወገዱ የሠላምና ፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ሠላም ደኅንነት ሊሰፍን ይችላል፡፡ ያኔ ደግሞ ወደ አምራች ኢንዱስትሪው በተለይም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚመጡት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በእጅጉ ሊጨምሩ ይችላል

ይህን ጥያቄ የሚመልስ ሥራ ከወዲሁ መሠራት ይኖርበታል፡፡ እንደ እኔ እንደ እኔ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ያለው ቦታ ውስን እየሆነ ባለበት ሁኔታ የባለሀብቶችን ጥያቄ መመለስና ዘርፉን አጠናክሮ ማስቀጠል ይከብዳል፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች መረጃ እንደጠቆመው፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከሚገኙ 177 ሼዶች መካከል አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን እየጠበቁ ያሉት 20 ብቻ ናቸው፤ 157ቱ ሼዶች በባለሃብቶች ተይዘዋል፡፡ አምስት ፓርኮች (አዳማ፣ ቦሌ ለሚ፣ አዲስ፣ ሰመራ እና ድሬዳዋ (የማኑፋክቸሪንግ ክፍሉ) በመሙላታቸው አዳዲስ ኢንቨስተሮችን ማስተናገድ አይችሉም፡፡

የኮርፖሬሽኑ ሼዶች በባለሀብቶች መያዛቸው አንድ ትልቅ ስኬት ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ገንብተው ባለሀብት ሳያገኙ የቀሩ ሀገሮች እንዳሉ ከሚገለጸው አኳያ ሲታይ ይህ አፈጻጸም ከፍተኛ ተብሎ የሚያዝ ነው፡፡


የኢንዱስትሪ ፓርኮች በቀጣይ የሚመጡ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብቶችን ለማስተናገድ የሚያስችል ሼድ የሌላቸው መሆኑ በኢንዱስትሪ ልማቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አያሳርፍም ተብሎ አይወሰድም፡፡ ኮርፖሬሽኑ ከወራት በፊት በወጣው መረጃ መሠረት በርካታ ሼዶችን እንደሚገነባ ጠቁሞ ነበር፡፡ ሼዶቹን ለመገንባት አሁን መንቀሳቀስ ቢጀምር እንኳ በቅርቡ ፓርኮቹን ሊፈልጉ የሚችሉ ባለሀብቶችን ማስናገድ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡

በሌላ መረጃ መንግሥት ፓርኮችን ለመገንባት ሀሳቡ እንደሌለው እየተገለጸ ነው፡፡ በቀጣይ ሊሆን የሚችለው የግሉ ዘርፍ ፓርኮቹን እየገነባ ለባለሀብቶች የሚያቀርብበት መንገድ መሆኑም ተመልክቷል። በግሉ ዘርፍ በኩል ግንባታዎች እንደሚካሄዱ የሚወጡ መረጃዎች የነበሩ ከመሆናቸው ውጪ እስከ አሁን ባለው ሁኔታ የቻይና ኩባንያ በዱከም ከገነባው ውጪ የኢንዱስትሪ ፓርክ መኖሩ ያጠራጥራል፡፡

መንግሥት ፓርኮቹ በግሉ ዘርፍ እንዲገነቡ አቅጣጫ አስቀምጦ ከሆነ ጥሩ ነው፤ የግል ዘርፉ ይገነባቸዋል ተብለው የሚታሰቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የወደፊቱን እንጂ በቅርቡ ሊከሰት የሚችለውን ፍላጎት ይመልሱታል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባለሀብቶች ለፓርኮቹ ያላቸው ፍላጎት ሲታይ ፓርኮቹ ልማት ላይ ፈጥኖ መሥራትን የግድ ይላል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን መገንባት ብዙ ሀብት ሊፈልግ ይችላል፡፡ እንደ ሀገር ይህን ማድረግ የሚቻል ላይሆን ቢችልም፣ ሊኖር ከሚችለው ፍላጎት አኳያ ከግሉ ዘርፍ የሚጠበቀው እንዳለ ሆኖ የኢንዱስትሪ ልማቱ የሚጠይቀውን ይህን መሰረተ ልማት ለመገንባቱ ሥራ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ ይህን በማድረግ የግሉን ዘርፍ የአምራች ዘርፍ ተሳትፎና ውጤታማነት ከእነግለቱ መጠበቅ ይቻላል፡፡

# ስፖርት



# የመንግሥት ተቋማት የስፖርት ለሁሉም ውድድር እየተካሄደ ነው

ብርሃን ፈይሳ

በ1990 ዓ.ም የተዘጋጀው የኢትዮጵያ የስፖርት ፖሊሲ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ማድረግ የዜጎች መሠረታዊ መብት መሆኑን ይጠቁማል። በትኩረት አቅጣጫውም ኅብረተሰቡ በሚኖርበት፣ በሚማርበትና በሚሰራበት አካባቢ በባህላዊ ስፖርቶችና በስፖርት ለሁሉም ተሳትፎውን የሚያጎለብትበትም ሁኔታ ይመቻቻል። ከአፈጻጸም ስልቶቹ መካከልም በመሥሪያ ቤቶች አካባቢ ከሠራተኛ ማህበራት ጋር የአሠራር ቅንጅት በመፍጠር በሥራ አካባቢ እንዲሁም በተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፍ ማድረግን ያካትታል። ከተሳትፎ ባለፈ የስፖርት ቡድኖችን በማቋቋም ማወዳደርንም ያበረታታል።

ይህም ሠራተኛውን በአካልና በአእምሮ በማብቃት አምራች ከማድረግም ባለፈ ማህበራዊ ግንኙነትን በማጠናከር፣ እርስ በእርስ በማስተዋወቅና በማቀራረብ አብሮ መስራትን ያጠናክራል። በመሆኑም በተለያዩ ዓለማት ሠራተኞች በስራቸው ላይ እያሉ ለደቂቃዎች አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ እንዲነቃቁ እንዲሁም የተለያዩ የእርስ በእርስ ውድድሮችን ያዘጋጃሉ። በኢትዮጵያም የመንግሥት ሠራተኞችን የሚያሳትፍ ዓመታዊ የስፖርት ውድድር በማዘጋጀት፤ ሠራተኛው አእምሯዊና አካላዊ ጤናውን ከመጠበቅ ባለፈ የመዝናኛና የእርስ በእርስ ግንኙነቱን ያጎለብትበታል።

ዘንድሮ ለ17ኛ ጊዜ የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች ስፖርት ለሁሉም ፌስቲቫል በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ካለፈው ሐሙስ ጀምሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል። በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አዘጋጅነት ከሚካሄዱ ዓመታዊ ውድድሮች መካከል አንዱ የፌዴራል ተቋማትን የሚያሳትፈው የስፖርት ለሁሉም መርሀ ግብር ነው።



ስፖርታዊ ውድድሮች የሠራተኛን አእምሯዊና አካላዊ ጤናን ከመጠበቅ ባለፈ ምርታማነትን ያሳድጋሉ፤

ለአንድ ወር በሚዘልቀው ውድድር በተለያዩ የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች የሚገኙ ሠራተኞችን የሚያፎካክር ሲሆን፤ ‹‹ስፖርት ለሁሉም ለሁሉም ስፖርት›› በሚል መሪ ሃሳብም ይታጀባል። በልዩ ልዩ ክንውኖች ከየካቲት 14/2016ዓ.ም መካሄድ የጀመረው ፌስቲቫሉ እስከ መጋቢት 24/2016 ዓ.ም ድረስ ከ25 በላይ ተቋማትን እንደሚያሳትፍ ከሚኒስቴሩ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

አዘጋጁ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚን ጨምሮ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት፣ ጤና ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክ ሚኒስቴር፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢንፎርሜሽንና መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ መከላከያ፣ ፌዴራል ፖሊስ... ከተሳታፊ ተቋማቱ መካከል ይገኙበታል።

ውድድሩ የተለያዩ አዝናኝ ጨዋታዎችን ጨምሮ አምስት የስፖርት ውድድሮች ይካሄዱበታል። እነዚህም እግር ኳስ፣ ቮሊቦል፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ቼዝ እና ዳርት ናቸው። በውድድሩ መክፈቻ ዕለት በውድድሩ አዘጋጅ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ እና ኢትዮ ቴሌኮም መካከል የእግር ኳስ ውድድር የተከናወነ ሲሆን፤ አንድ አቻ በሆነ ውጤት መለያየት ችለዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ የሚደረገው ይህ ውድድር ከተጠናቀቀ በኋላም በሀገር አቀፍ ደረጃ የመንግሥት ተቋማት የስፖርት ለሁሉም ውድድርን ለማከናወን ታቅዷል። ውድድሩን አስመልክቶም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ ሠራተኛው ጤናማ፣ ምርታማ እና ግንኙነቱም ውጤታማ ሳይሆን ሀገር የምትፈልገውን የእድገት ደረጃ ማስመዝገብ የማይቻል መሆኑን ይጠቁማሉ።

የፌዴራል ተቋማት የስፖርት ውድድር በሙያተኞች እየታገዘ ላለፉት 16 ዓመታት ቢካሄድም የዘንድሮው ግን በተለያዩ ሀገራዊና ወቅታዊ ሁኔታዎች ውስጥ የሚደረግ በመሆኑ የሚጠበቀውን ያህል ተሳታፊ አልተገኘም። ይህን መሰል ውድድሮች በዓለም አቀፍ ስፖርት መርህ ውስጥ ስፖርት ለሁሉም በሚል ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን፤ በኢትዮጵያም በስፖርት ልማት መርሆችና የስፖርት ፖሊሲ ውስጥ ኅብረተሰቡ በሚኖርበት፣ በሚማርበትና በሚሰራበት አካባቢ በስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ታስቦ ይሠራል።

ይህ ተግባራዊ ከሚደረግባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የሆነው የመንግሥት ሠራተኞች ውድድር ውጤታማ የሥራ ክንውን እንዲኖራቸው የሚያግዝ ነው። ይኸውም የአንድ ተቋም ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሁሉም ተቋማት ተግባር መሆንም ይገባዋል። ከዚህ ባለፈ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመላው ኢትዮጵያ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የስፖርት ውድድር ለማካሄድ በተደጋጋሚ ጥረት ቢደረግም ባጋጠሙ ችግሮች ምክንያት ሳይሳካ ቀርቷል። ዘንድሮም የሁሉንም ክልሎችን ያሳተፈ ውድድር ለማከናወን በትኩረት የሚሠራ መሆኑንም ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸዋል።


## INVITATION FOR A BIDS

**TO: ALL Car rent, Vehicles Insurance Hotel Service Providers and Construction materials, water supply and farm tools suppliers**

PIN (PEOPLE IN NEED), an international NGO, invites for submission of sealed Technical & Financial Company Profiles from eligible bidders for providing of the below listed service and materials; Car rent service, Hotel service, Construction materials, water supply and Farm tools materials for PIN Various project:

ALL Service providers and general Trading's supplier who have valid license for the current year can collect the tender documentation in PIN office in Hawassa (Kebele 05 behind Central Hotel), tel. 0462123135 or 0462122140 or Addis Ababa, Yeka sub-city, Kebele 13/14 house no 904 Tel. Tel 0116185121 or 011 662 0503 or send the request by procurement.ethiopia@peopleinneed.cz from until 15/03/2024 during working days.

Question and any clarification relating to this tender, should be sent to the following email address: procurement.ethiopia@peopleinneed.cz until 18/03/2024. If PIN answers the question, all other tenderers will be copied the answer. Communication will be held through e-mail. Questions could be answered only until 19/03/2024. PIN does not guarantee that all questions will be answered.

Tender offers to be submitted to PIN or sent by registered post to reach the PIN office before closing date and time: 26,27,28 March 2024, 3:00 PM (Local time Afternoon 9:00) Car Rent, Vehicles Insurance, Hotel service and Construction, water supply and farm tools respectively to following address: Hawassa office, Haike dare sub-city, in 05 Kebele (Directly behind Central Hawassa Hotel Building PIN Addis Abeba Office, Yeka Sub-City, kebeles 13/14, house no.904. Bids received after the closing date & time will not be considered.

Envelope opening session will be held on 26, 27,28, 29 March 2024, 3:30 PM (Afternoon 9:30 local time) for Car Rent, Vehicles Insurance, Hotel service, and (Construction materials, water supply and farm tools) respectively: Hawassa office, Haike dare sub-city, in 05 Kebele (Directly behind Central Hawassa Hotel Building) and PIN Addis Abeba Office, Yeka Sub-City, kebeles 13/14, house no.904 based on the submitted bids. The tenderers or their authorized representatives are invited to be present at the envelope opening.

For more information please communicate by the address of procurement.ethiopia@peopleinneed.cz. Optionally, PIN office in Hawassa (Kebele 05 in behind Central Hotel) tell +251462123135, +251462124024, 0955457940 and Addis Ababa, Yeka sub-city, Kebele 13/14 house No. 904 tell 01116620503, 01116185121.

PIN Ethiopia reserves the right to accept or reject any or all bids.

**PIN (PEOPLE IN NEED)**